ሚያዝያ 14 ቀን 2006 ዓ.ም

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች

2005 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

አጭር መግለጫ

የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 18 እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ (Protection of Basic Services) ፕሮግራም የሰጠውን የበጀት ድጋፍና ድጎማ ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፤ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፤ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ፣ በዚሁ መሠረት በ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትና በተመረጡ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲቶች ዕቅድ ክንውን ሪፖርት እና የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮግራም ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ (Protection of Basic Services) ተከታታይ እና ማጠቃለያ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች ናቸው፡

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በመ/ቤታችን የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን በውጭ እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያካትታል፡፡

3. የ2005 በጀት ዓመት የተለያዩ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው፡፡

4. የ2005 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች እንዲሁም በ20 የክዋኔ ኦዲት ጥረዞች ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ፣ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹም ቅጅ 2 ጥራዞች ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ በአብዛኛው የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉም ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች

ሲሆኑ፣ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የ2005 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሣብ ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊኒት ኦዲትን በተመለከተ

7. የ2005 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ የኦዲት ዕቅዳችን መሠረት ያደረገው እንደተለመደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትንና አዲሱን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 63/2 መሠረት የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሂሳባቸውን በመዝጋት ለኦዲት ማቅረብ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በሌላም በኩል መ/ቤታችንም በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች ሂሳባቸውን ዘግተው ሲያቀርቡ ኦዲቱን በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ታህሣሥ 30 በማጠናቀቅ ሪፖርቱን ለኦዲት ተደራጊዎች ለመስጠት ግብ ጥሏል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችለው የኦዲት ካላንደርና ዘዴ ላይ ለውጥ በማድረግ ኦዲቱ የሂሳብ መዝጋትን ሳይጠብቅ በየዓመቱ በጥር ወር ተጀምሮ በተከታዩ ዓመት ታህሣሥ ላይ የሚጠናቀቅበት ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ ይታወሳል፡፡

8. በዚሁ መሠረት በ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 140 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 132 መ/ቤቶችን በፌዴራል ዋና ኦዲተር የተቀሩትን ስምንቱን ደግሞ በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ መታቀዱ ይታወሳል፡፡ በመ/ቤታችን በኩል ኦዲት ለማድረግ ከታቀዱት 132 መ/ቤቶች ውስጥ 130 እንደዚሁም በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን በኩል ኦዲት ለማስደረግ የታቀዱት 8 በድምሩ የ138 የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በመከናወኑ የፋይናንስና ህጋዊነት የኦዲት ሽፋኑን 98.57% ለማድረስ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በመ/ቤታችን በኩል ተገቢው ጥረት ቢደረግም የብሄራዊ ትያትር የ2005 በጀት ዓመት ሒሳቡን ሊዘጋ ባለመቻሉ እንደዚሁም የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የተፈቀደለትን በጀት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት

ሚኒስቴር ጠይቆ ባለመጠቀሙና የሂሳብ መዛግብትም ባለማዘጋጀቱ ኦዲቱን ማከናወን አልተቻለም፡፡

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

9. የ2005 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን በ132 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ281 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ	በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲት		አጠቃላይ	
	2004	2005	2004	2005	2004	2005
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው	49	59	13	1	62	60
ከጥቅት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌት ያለበት አስተያየት	48	49	270	280	318	328
አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለጽ አስተያየት የተሰጠባቸው	6	7			6	7
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	13	15			13	15
ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለመዝጋታቸው አስተያየት ያልተሰጠባቸው	1	2			1	2
ድምር	**117**	**132**	**283**	**281**	**400**	**413**

በፌዴራል መንግሥት የልዩ ልዩ መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

10. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር ሕጉን፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅድው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከደንብና መመሪያ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የተገኙ ሲሆን፤ የም/ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ ይገባል ተብሎ የታመነባቸው አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርቧል::

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

11. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አጠባበቅ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ5 መ/ቤቶች ብር 1,272,093.33 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተገኘባቸው ጂማ፤ ሰመረ፤ ወሎ፤ ባህር ዳርና ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተገቢው እርምጃ ተወስዶ እንዲተካ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

12. በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ3 መ/ቤቶች (ደብረ ማርቆስና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እና አላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ) ቆጠራው በብር 997,412.79 ልዩነት በማነስ የታየ ሲሆን በአጠቃላይ በ24 መ/ቤቶችም የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንደሚታዩ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

13. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቦች ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ብክነት፤ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በቆጠረ ከተገኘው ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ፤ በማነስና በመብለጥ የታየው ልዩነትም ተጣርቶ እንዲተካ ወይም ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ እና በ24ቱ

መ/ቤቶችም የታዩ የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዲስተካከሉ አሳስበናል፡፡

የውዝፍ ተሰባሳቢ ሂሣብ

14. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናነስ አስተዳዳር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ77 መ/ቤቶች ብር 877,045,264.30 በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

15. ከዚህ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ማስተባበሪያ ብር 173,607,265.52፣ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር 149,427,709.65፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 100,298,362.09፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 97,146,944.59፣ ግብርና ሚ/ር ብር 77,744,994.72፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 32,153,328.69፣ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 26,671,151.92 እና የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 22,945,234.57 ይገኙበታል፡፡

16. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣቡ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በወቅቱ ካልተወራረደ ወይም ካልተሰበሰበ በቆየ ቁጥር የመሰበሰብና ወደ ሀብትነት የመለወጥ እድሉ ተዳክሞ ለብክነት በር የሚከፍት በመሆኑ መ/ቤቶቹ የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው ገንዘቡን እንዲሰበስቡ ወይም እንዲያወራርዱ አሳስበናል፡፡

በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ዋና ዋና የአሠራር ችግሮች

17. የተሰብሳብ ሂሳብ አያያዝ የፋይናንስ ደንቡን የተከተለ መሆኑ ሲጣራ በ8 መ/ቤቶች ከታዩ የአሰራር ችግሮች ዋና ዋናዎቹ፣

   - በአብዛኛዎቹ መ/ቤቶች ለእቃ ግዥ ሰራተኞችና ሌሎች ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በተደጋጋሚ የሚሰጥ በመሆኑና በእያንዳንዱ የእቃ ግዥ ሰራተኛ ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ ዕዳው ከማን እንደሚፈለግ ዝርዝር ማስረጃ ባለመኖሩ ከሰራተኛው የሚፈለገውን ቀሪ እዳ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
   - በአንዳንድ መ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ ቢያዝም የተሰብሳቢ ሂሳብ ሠነዱ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑና ከመቼ ጀምሮ የሚፈልግ ሂሳብ እንደሆነ

የሚገልጽ ማስረጃ እና ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- ➢ በበርካታ መ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባልተለመደ ሚዛን /Abnormal balance/ በክሬዲት አቅጣጫ መሆኑ፤
- ➢ ተሳብሳቢ ሂሳቡን በሌላ የሂሳብ መደብ የመመዝገብ ሁኔታ በበርካታ መ/ቤቶች የሚስተወሉ፣ በወጪ ተመዝግቦ እያለ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት የተደረገ ሂሳብ መገኘቱ፣

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

18. በመሆኑም ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግለቸው፤ ተቀፅላ ሌጀር የሌላቸው እንዲመሠረትላቸው፤ ማስረጃ የሌላቸው ማስረጃ ተሟልቶላቸው እንዲያዙ እና ለወደፊቱ ባልተሟላ ማስረጃ ሪፖርት እንዳይዘጋጅ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የገቢ ሂሣብ

19. የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝቷል፡፡

በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ

20. የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ32 መ/ቤቶችና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 32,139,625.90 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ ተገኝቷል።

21. በአዋጁ በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ምዕራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 11,583,879.14፣ አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,469,351.03፤

ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,223,745.32 እና ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,588,619.20 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

22. የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Coustom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

23. በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

24. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 286,818,836.06 እና በሌሎች 4 መ/ቤቶች ብር 39,856,103.92 በድምሩ ብር 326,674,939.98 ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

25. ውዝፍ ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 252,299,705.34፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 19,512,045.63፤ መቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 13,134,569.83፤ ጅማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,850,496.24፤

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 36,389,175.05፣ እና የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብር 3,342,102.41 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

26. በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

27. በበጀት ዓመቱ ገቢን እንዲሰበስቡ በተፈቀደላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች (መቱ፤ ጅግጅጋ፤ አዳማና ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጄክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት) የተሰበሰበው የውስጥ ገቢ ብር 69,356,951.10 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም 7 መ/ቤቶች (መቀሌ፤ ሚዛን ቴፒ፤ ባህር ዳር፤ መዳ ወላቡ፤ ሰመረና ወሎ ዩኒቨርሲቲዎች እና አላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ) መጠኑ ያልታወቀና በገንዘብ ያልተገለፀ የውስጥ ገቢ ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች የሚሰበስቡ ቢሆንም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት የማያደርጉ የውስጥ ገቢውንም መዝግበው የማይይዙ መሆኑ ታውቋል፡፡

28. ይህ አሰራር በመ/ቤቶቹ በራሳቸው የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎችና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪም ሂሳብም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

29. በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ማንኛውም የመንግስት ገቢ ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲሰበስቡና በሂሳብ መግለጫዎቻቸውም በመካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ ነገር ግን ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በማይወስዱ፤ የመንግሥትን ገቢ ሰብስበው መዝገብ የማይይዙና የሚደብቁ መ/ቤቶች ላይ መንግሥት ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

30. የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሥር ባሉ ሦስት ቅ/ጽ/ቤቶችና በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 42,942,143.14 እና በሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት /የ5 ዲክለራሲዮን/ እና በሌሎች 5 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የገቢ ሂሳብ የገቢ ታሪፍ/ የማስከፈያ ተመን ባለመኖሩ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያትና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፣ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል።

31. ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

32. የገቢ ሂሳብ ተከታታይ የገቢ ደረሰኝ ተዘጋጅቶለት በትክክል መሰብሰቡን እና መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ6 መ/ቤቶች ብር 2,164,212.26 እና በሌሎች 3 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

33. ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጎድል ወይም እንዲጣፋ መንገድ ይከፍታል፡፡ በመሆኑም ከላይ ለተመለከተው ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ እንዲዘጋጅለትና ሌሎችም ገቢ የሚደረግ ሂሳብ ደረሰኝ ተዘገጅቶለት መመዝገብ እንደሚገባ ለመ/ቤቶቹ አሳስበናል፡፡

በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

34. በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

35. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 54 እና 55 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ

በተደነገገው የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መዉጣት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃው አገር ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ዉስጥ እቃው ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መልኩ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 2,840,773 እንዲሁም በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 219,683,687.83 በድምሩ ብር 222,524,461 ዋስትናውን ከሰጠው ድርጅት ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፣ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 35 መሠረት ለመንግሥት መ/ቤት በስህተት ገቢ የተደረገ ሂሣብ መኖሩ ሲረጋገጥ ገንዘቡ ለባለመብቱ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በናሙና ከታዩት ውስጥ ፡-

- ✓ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 976,135.67፣
- ✓ በቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 14,056,107.58 በድምሩ ብር 15,032,243.25 ከሁለቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በ2005 በጀት ዓመት ተመላሽ የተደረገው ሂሣብ አስቀድሞ በገቢ የተመዘገበና ለከፋዩ ተመላሽ የተደረገ ሂሣብ ማስተካከያ ሳይደረግበት በዘመኑ የተሰበሰበው ትክክለኛ ገቢ ጋር ተዳምሮ እየተመዘገበ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
  - ➢ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት አስመጪዉ ወይም ወኪሉ የጉምሩክ ዲክላራስዮን ከቀረበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት ቀን ድረስ ቀጣዩን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ካልፈፀመ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ያዛል፡፡ ነገር ግን በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር

883,692.79 ቀረጥና ታክስ የያዙ ዲክላራሲዮኖች ተመዝግበው ቀጣዩን የጉምሩክ ስነስርዓት ሳይፈጽሙ ወይም ሳይሰረዙ ከአንድ እስከ አራት አመት ቆይተው ተገኝቷል፡፡

37. በመሆኑም የመንግስት ገቢ የመንግስት የገቢ አዋጆች፣ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ ገቢው እንዲሰበሰብ እናሳስባለን፡፡

የወጪ ሂሣብ

38. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውናመጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሣቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ

39. በወጪ ለተመዘገቡ ሂሣቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ25 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 202,587,739.10 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

40. ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት ብቻ የተፈፀመ ክፍያ፣ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሣቦች ጎላ ያሉት ናቸው፡፡

41. ማንኛውም ሂሣብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያ መሠረት ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት እናሳስባለን፡፡

የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች

42. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ43 መ/ቤቶች ብር 165,892,637.56

የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

43. ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ በሀርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 32,061,100.00፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,117,878.73፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 18,344,467.23፣ ማዕድን ሚ/ር ብር 16,274,515.25 እና አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 14,168,410.69 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

44. ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ መፈጸም ያለበትን ግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸም እና የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ተግባራዊ የሚሆነው ግልጽ ጨረታ ሁለት ጊዜ ወጥቶ እቃው በሚፈለገው ጥራትና መጠን ካልተገኘ ቢያንስ አምስት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ መጋበዝ የሚለውን ሳያሟሉ ግልጽ ጨረታ ያላወጡና በውስን ጨረታው የግዥ ዘዴ በቂ አቅራቢዎች ሳይጋብዙ ግዥን ማከናወን የሚሉት ይገኙበታል፡፡

45. የግዢ መመሪያን ሳይከተሉ ግዢ መፈጸም ለምዝበራና ለጥራት መጓደል ጭምር የሚያጋልጥ በመሆኑ የመንግሥት ግዢ ደንብና መመሪያን አክብረው በማይሠሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

46. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ41 መ/ቤቶች ብር 75,992,434.84 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል።

47. ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,000,000.00፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ 10,196,507.81፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 8,605,050.51፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,190,691.01 ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,062,182.75 እና ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,956,941.47 ሲሆን፣ ከምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና የአልጋና የምግብ ወጪያቸው በመ/ቤቱ ተሸፍኖ እያለ

የውሎ አበል በመክፈልና እና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የሃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለዩኒቨርሲቲ የስራ አመራሮች ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለለቀቁና ሥራ ላይ ላሌሉ ሰራተኞች ክፍያ መፈጸምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

48. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሣብ ተመላሽ እንዲሆንና ለወደፊቱም ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

49. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ በደንብና በመመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ13 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 230,819,512.43 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡

50. ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 102,872,461.13፤ የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ብር 51,883,514.72፤ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 43,983,869.27 እና የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ብር 13,000,000.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

51. ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለበቸው፡፡ ነገር ግን ተገቢውና ጠንካራ ክትትል ካልተደረገ በቀር በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ ባክኖ የመቅረት ዕድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡ በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

በብልጫ የተከፈለ ወጪ

52. በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ በ10 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግዢዎች ብር

1,943,820.40 እና በ7 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 2,527,401.22 በጠቅላላው ብር 4,471,221.62 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

53. በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፣ በድገሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈል፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይገኝ የቤት አበል የደመወዝ ጭማሪና ጥቅማ ጥቅሞችን መክፈል የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ስለሆነም ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ አግባብ ባለመሆኑ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት

54. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ10 መ/ቤቶች በብር 22,557,742.81 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል::

55. ከዚህም ውስጥ ትምህርት ሚ/ር ብር 19,231,147.66፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,597,312.92 እና ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 795,550.00 ግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሲሆኑ በሌሎች በ7 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 1,557,178,357.45 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው ናቸው፡፡ ከዚህም ውስጥ በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ብር 785,919,809.52፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 549,166,140.13፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 157,971,920.15፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 48,756,934.71 እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ብር 10.08 ሚሊዮን ይገኝበታል፡፡

56. የዚህ ዓይነት አሠራር ለንብረት ብክነት ስለሚያጋልጥ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች ለየመ/ቤቶቹ አገልግሎት ለመዋላቸው በማስረጃ እንዲረጋገጥ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የወጪ ማስረጃ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ

57. በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ23 መ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 90,973,122.91 ተገኝቷል፡፡

58. የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሳብ ሂሣብ ውስጥ ጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 48,055,198.58፣ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 17,778,644.44፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 10,258,169.01 እና አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,421,520.70 እና መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 2.66 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

59. በመሆኑም የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንዲቀርብለት፣ አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

60. ከውስጥ ገቢ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸው ያወጡትን ወጪ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት አካተው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያቀርቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ3 መ/ቤቶች ብቻ ከውስጥ ገቢያቸው ወጪ ያደረጉት ብር 22,265,251.22 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ /በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ/ መሆኑ ታውቋል፡፡

61. ከዚህም በተጨማሪ የውስጥ ገቢ ሂሳባቸውን በሪፖርት የማያካትቱ መ/ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት /አባሪ-10 ይመልከቱ/ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት እንደማያደርጉ ታውቋል፡፡ ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ የመ/ቤቶቹን ትክክለኛውን የፋይናንስ አፈጻጸምና ገፅታ እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

62. በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ከገቢው ላይ የሚደረግ ማንኛውም ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

63. ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ባለፉት ዓመታት ሪፖታችንም በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት ብናሳስብም ሊታረም ባለመቻሉ በም/ቤቱ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>በመስክ ላይ ለነበሩ ነገር ግን ለግንባታ ላልዋሉ የግንባታ ዕቃዎች (Material on Site) የተፈጸመ ክፍያ፤</u>

64. በፌዴራል የመንግሥት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት በሳይት ላይ ያሉ ዕቃዎች በገንዘብ እንዲተካ የማይፈቀድ ቢሆንም በ11 መ/ቤቶች በሳይት ለሚገኙ ዕቃዎች ብር 168,570,095.60 ለተለያዩ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች የግዢ መመሪያውን በመጣስ በገንዘብ እንዲተካ ከመደረጉም በተጨማሪም በ4 መ/ቤቶች ብር 18,281,997.57 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከእያንዳንዱ ክፍያ ተቀንሶ ለመንግሥት ካዝና ተመላሽ መሆን ሲገባው ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

65. በሌላ በኩል ከፍተኛ ግንባታዎችን የሚያከናወኑ መ/ቤቶች በውል በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ግንባታውን በማያጠናቅቁት ተቋራጮች ላይ የጉዳት ካሳ ጥያቄ በማቅረብ ከተቋራጮቹ የጉዳት ካሣ የማይሰበስቡ መሆኑ ታውቋል።

66. በመሆኑም ያልተሰበሰበው ብድር እንዲሰበሰብ፤ የግዢ ህጉን በመጣስ በሳይት ላለ የግንባታ ግብዓቶች በገንዘብ የተተከው ጥብቅ ቁጥጥር ተደርጎ ግብዓቱ ለግንባታ መዋሉ እንዲረጋገጥ፤ ለወደፊቱ ግን መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ብቻ እንዲፈፀም በሪፖርታችን አሳስበናል።

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

67. በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ46 መ/ቤቶች ብር 471,620,351.75 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

68. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 221,664,033.96፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 148,635,332.93፣ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 21,255,177.05፣ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 16,930,809.30፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,141,502.19፣ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,184,429.01 እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,995,439.11 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

69. በተጨማሪም በ8 መ/ቤቶች የተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ችግር ያለባቸው፣ ያለበቂ ማስረጃ በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገቡ፣ ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ ያልተቻለ፣ በተከፋይ ሂሳብ መግለጫ ያልተካተቱ፣ እንዲሁም ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የሚያሳዩ ተከፋይ ሂሳቦች ተገኝተው አስፈላጊው ማስረጃ እንዲቀርብና ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግላቸው ለየመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ የሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

የበጀት አጠቃቀም

ከበጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ

70. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት በ30 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱና የበጀት ዝውውር ሣይፈፅሙ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 379,901,964.67 ተገኝቷል፡፡

71. ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች መካከል ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 96,047,945.95፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 48,117,768.20፣ ጎንደር

ዩኒቨርሲቲ ብር 21,800,000፣ ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 44,200,479.61፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 40,633,615.89 እና አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,712,828.14 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

72. በመሆኑም መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ እንደዚሁም በበጀት አዋጁ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

73. የተፈቀው በጀት በትክክል ሥራ ላይ ለመዋሉ ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሣብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ96 መ/ቤቶች ብር 2,259,197,962.73 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም 9 መ/ቤቶች ብር 49,594,003.86 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሳይፈቀድ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ ወጪ ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

74. ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ብር 213,835,430.84፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 119,943,791.03፣ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 110,533,882.82፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 86,413,575.05፣ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 68,490,363.94 የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 62,189,884.33፣ የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር 66,166,058.74 እና ኢንዱስትሪ ሚ/ር ብር 53,393,010.81 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

75. ለወደፊቱ መ/ቤቶች የሚያቀርቡት የበጀት ጥያቄ በጥናት ላይ እንዲመሠረትና ከተፈቀደም በኋላ ተገቢውን ክትትል በማድረግ የተፈቀደላቸውን በጀት ሥራ ላይ ለማዋል ጥረት እንዲደረግ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የንብረት አስተዳደር

76. መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር በዚህም ዓመት አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ፣

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	28 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱ ያላረጋገጡ	13 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	17 መ/ቤቶች
የቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	32 መ/ቤቶች
ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረት የተገኙባቸው	23 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	47 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	16 መ/ቤቶች

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

77. በተጨማሪም በ10 መ/ቤቶች የተለያዩ ከፍተኛ የንብረት አያያዝና አስተዳደር የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች የሚታይባቸውና ቀደም ባሉት የኦዲት ሪፖርታችንም እንዲያስተካክሉ አስተያየት ተሰጥቶባቸው አሁንም ያልተስተካከሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

78. በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲመራ፤ በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ፤ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

79. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ16 መ/ቤቶች	177 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ34 መ/ቤቶች	298 ተሽከርካሪዎች
በተለያዩ ድርጅቶች ሥም ሊቢሬ ያላቸው ወደ መ/ቤቱ ስም ያልተቀየረላቸው	በ7 መ/ቤት	25 ተሽከርካሪዎች
የሻንሲና ሞተር ቁጥር ከሊብሬው የማይገጥም፣	በ2 መ/ቤቶች	6 ተሽከርካሪዎች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ2 መ/ቤቶች	5 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡

80. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ፣ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው በመግለጽ፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ፣ ሊብሬ ያልቀረበላቸው አስፈላጊው ማስረጃ ተሟልቶ እንዲወጣላቸው፣ በሌላ መ/ቤት የተያዙት ሊብሬ በባለቤትነት ወደዚያው መ/ቤት እንዲቀየርላቸው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

<u>መሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ</u>

81. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጄክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍነው የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርና፣ የውሃና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

82. የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ PBS II ስምምነትን ተከትሎ በተሻሻለው የኦዲት ስምምነት መሠረት ተከታታይ ኦዲቱ በህጋዊነት (Fiduciary Responsibility) ላይ እንዲያተኩር ተደርጎ፣ የኦዲት ውጤቱ የፕሮጄክቱ ሂሣብ ዓመታዊ ኦዲት አካል እንዲሆን በተወሰነው መሰረት ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

83. በዚህም መሠረት ከሁሉም ክልሎች በናሙና በተመረጡ በ298 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ የክልል ሴክተር ቢሮዎች ተከታታይ ኦዲት (Continuous Audit) እና አንድ ፕሮግራም አቀፍ የሆነ የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ በ281(94.3%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የሴክተር ቢሮዎች እንደዚሁም ፕሮግራም አቀፍ የሆነውን የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደረጃ ለመፈጸም ተችሏል፡፡ የተከታታይ ኦዲቱ አፈፃፀም ከታቀደው ሊያንስ የቻለው በዕቅድ ያልተያዙ በሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽንና በፍርድ ቤቶች ጥያቄ በርካታ ልዩ ኦዲቶች በመከናወናቸው ነው፡፡

<u>የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ</u>

<u>ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ</u>

84. በገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ የ2005 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ የተላከ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት የታዩት ዋና ዋና ግኝቶች ደግሞ የሚከተሉተ ናቸው፡፡

85. በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በተለያየ ምክንያት(በዋጋ ወይም በታሪፍ አመዳደብ ወዘተ) በስህተት የተሰበሰበ ቀረጥ ግብር ከፋዩ በስህተት የከፈለ ለመሆኑ ሲታወቅና በኮሚቴ ሲረጋገጥ በስህተት የተከፈለው ቀረጥ ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግለት ሲሆን በ2005 በጀት አመት ለቀረጥ ተመላሽ የተደረገው በገቢ ተመላሽ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ሪፖርት ተመዝግቦ ለሚኒስቴሩ በመቅረቡና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ይህንኑ ሂሳብ በማጠቃለሉ የተጠቃለለው የገቢ ሪፖርትም በዚያው መጠን ሚዛኑ ከፍ (overstated) እንዲል እየተደረገ መሆኑ፣

86. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትሬዠሪ አካውንት ክፍያ ለመፈጸሙም ሆነ ወደ ትሬዠሪ አካውንት ገንዘብ ለመግባቱ መረጃ ሲደርሰው ተገቢው ማዘዣ ሳይሞላ በባንክ አድቫይስ ላይ ብቻ ምዝገባው በማሳለፍ የሚመዘገብ መሆኑና በፋይናንስ ደንቡ መሰረት ለእያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ የምዝገባ ማዘዣ እየተዘጋጀ ለትክክለኛነቱም በሚመለከተው አካል እየተረጋገጠ ምዝገባው መከናወን

እንዳለበት በባለፉት ኦዲት ሪፖርት በተደጋጋሚ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በ2005 በጀት ዓመትም እርምጃ ሳይወሰድ በአድቫይሱ ብቻ ምዝገባ መከናወኑ፣

የክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች በተመለከተ

87. የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትን ተከትሎ መ/ቤታችን የፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲቱን ሽፋንና ጥራት በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በሂደት ትኩረቱን በክዋኔ ኦዲት ላይ የማድረግ አቅጣጫን ለመከተል በመወሰነው መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጄክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መምታተቸውን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል፡፡

88. በዚሁ መሠረት ከጥር 2005 በፊት ተጀምረው የዝርዝር ኦዲት ስራቸው ወደዚህኛው የኦዲት አመት የዞሩ 10፣ ከጥር 2005 በኋላ ተጀምረው እስከ ታህሣስ 30 የሚጠናቀቁ 10 እንደዚሁም ኦዲታቸው ተጀምሮ ወደ ተከታይ ዓመት የሚሻገሩ 8 በድምሩ 28 የክዋኔ ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡

89. የእቅድ ዘመኑ የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻፀም ሲታይ ካለፈው ዓመት የዞሩትን 10 ኦዲቶችን ጨምሮ በዚህ የእቅድ ዘመን ወጪ መደረግ ከሚገባቸው 20 የክዋኔ ኦዲት ሪፖረቶች ውስጥ የሃያዎቹም ሥራቸው ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶቹ የተላከ ሲሆን የ6 ክዋኔ ኦዲቶች ሥራቸው ተጀምሮ በተለያየ የኦዲት ደረጃ ላይ ሆኖ ወደ ቀጣዩ ዓመት ተላልፏል፡፡ በዚህም መሠረት የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ ክንውን አፈፃፀም 100% ሆኗል፡፡ ይሁንና ኦዲተሮቻችን ባደረጉት ከፍተኛ ጥረትና ግፍት የታቀደውን መፈጸም ቢቻልም የኦዲቶቹ የጥራት ጉዳይ አሁንም ሰፊ ሥራና ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ ተገቢውን ትኩረትና ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል፡፡

90. ኦዲታቸው የተጠናቀቁት 20 የክዋኔና ኦዲቶች ዋና ዋና ግኝቶች ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የታክስ መረጃ አያያዝንና አስተዳደርን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

91. ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ግብር ከፋዮች መረጃ በጥራትና በተቀላጠፈ መልኩ በዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አስተዳደር ለመያዝ የሚያስችል የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS)፣ በእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተያዘ መረጃን የሚመዘግብና የሚቆጣጠር፣ የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥርና የጣት አሻራ መመዝገቢያ እና የጉምሩክ ቀረጥ አከፋፈልን የሚያግዝ አሲኩዳ የተባለ የመረጃ ቴክኖሎጂ የዘረጋ ቢሆንም በዘረጋው የመረጃ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ በአግባቡ የግብር ከፋዩን መረጃ አሰባስቦ የመያዝ የማደራጀት እና የማስተዳደር ተግባሩን በቂ ትኩረት በመስጠት ተግባራዊ አለማድረጉ፤

92. በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) በማዕከል ተመዝግቦ የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ በቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች (የታክስ ማእከል) ተመዝግቦ ከተያዘው የግብር ከፋይ መረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆን ሲገባው በማዕከል በተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) በአምስቱ ቅርንጫፎች ያሉ ተብሎ ተመዘገቦ የተያዘው 29792 ግብር ከፋዮች ሲሆን በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት አምስቱ የታክስ ማዕከላት ግን በተጨባጭ በግብር ከፋይነት ተመዝግበው የተያዙት 21595 ግብር ከፋዮች ብቻ ሲሆን ይህም በማእከል በSIGTAS ተመዝግቦ ከተያዘው በ8197 የሚያንስ መሆኑ፤

93. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮች በሙሉ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መርሃ- ግብር መሰረት መሳሪያውን መጠቀም የሚኖርባቸው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዮት በከፍተኛ ግብር ከፋዮች በባህርዳር፣ በሀዋሳ፣ በምዕራብና በምስራቅ አ/አ ቅ/ጽ/ቤቶች በSIGTAS ተመዝግበው ከተያዙት 29792 ግብር ከፋዮች ውስጥ 17702 (59.41%) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የማይጠቀሙ መሆኑ፣

94. ግብር ከፋዩ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎች ገዝቶ ከሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች በአማካይ በዓመት 15670 የሚሆኑት በብልሽት ምክንይት ለጥገና

የሚገቡ ሲሆን 7146 (46%) በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው ሲወጡ የተቀሩት 8320 (54%) በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው እንደማይወጡ፣ አገልግሎት ላይ ከዋሉ ከአንድ አመት በላይ የሆናቸው 72964 የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ዓመታዊ ምርምራ በተሟላ መልኩ እንደማይደረግላቸው እና ባለሥልጣን መ/ቤቱም በህጉ እና በገቡት ግዴታ መሰረት ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎችን በመከታተልና በመቆጣጠር እርምጃ የማይወስድ መሆኑ፤

95. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተመዘገቡ የሽያጭ መረጃዎች ወደ መረጃ ቋት መተላለፍ አለመተላለፋቸው በየታክስ ማዕከሉም ሆነ በዋናው መ/ቤት ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የሚቻልበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ሲገባው አለመደረጉ፣

96. የሽያጭ መመዝግቢያ መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ መዋል ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ እስከ 2005 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ለግብር ከፋዩ ከተሸጡት 82141 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ውስጥ 72964 (89%) አገልግሎት ላይ የዋሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 8755 (12%) ብቻ የሽያጭ መረጃን ወደ መረጃ ቋት የሚያስተላልፉ ሲሆኑ፣ የተቀሩት 64209 (88%) የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሽያጭ መረጃን ወደ መረጃ ቋት የማያስተላልፉ መሆኑን፣ እና 5888 (12%) የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ከሲስተሙ ጋር ያልተያያዙ መሆናቸው፡

97. ሥራ አቁመዋል ተብለው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፋይላቸው የተዘጉ ተብለው ከተያዙት 3362 ግብር ከፋዮች ውስጥ ሥራ እንዳቆሙ በማዕከል ደረጃ የሚታወቁት እና የተዘጉ ተብሎ በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) ላይ የሚታዩት 1504 ሲሆኑ ቀሪዎቹ 1858 ግብር ከፋዮች ግን በሥራ ላይ (active) እንደሆኑ የሚታይ መሆኑ፤

በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደርን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

98. የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎች በውስጣቸው መሰረታዊ አገልግሎቶችን (የእሳት አደጋ ማጥፊያ፣ መጸዳጃዎች፣ መጠለያ፣ የካፍቴሪያ ወዘተ…) በሚሟላት ተጠቃሚዎች ያለችግር አገልግሎቶችን ሊያገኙ የሚገባ ቢሆንም በኦዲቱ

በናሙና ከታዩት መናኸሪያዎች ውስጥ የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፤ የቃሊቲ እና የድሬዳዋ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና ሻሸመኔ ከተማ መናኸሪያዎች ግቢ ውስጥ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ እና ለጠፉ ንብረቶች ማቆያ ቦታ እና የተሟላ የመፀዳጃ ቤቶች የሌላቸው ሲሆን፤ የድሬዳዋ፣ የሐዋሳ እና የአዳማ መናኸሪያዎች የመንገደኞች ማረፊያና መጠበቂያ መጠለያ ቦታ ቢኖራቸውም መቀመጫ ወንበር የሌላቸው መሆኑና የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፣ የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች እና የሻሸመኔ መናኸሪያ ከነጭራሹ ለተገልጋዮች የመጠለያ ቦታ የሌላቸው መሆኑ፣

99. ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት ለተሳፋሪዎች መረጃ የሚሰጥበት፣ ለአካል ጉዳተኞችና አቅመ ደካሞች መግቢያና መውጫ ቦታዎች፣ ሸኚ በማይገባበት ቦታ የዕቃ መግፊያ ጋሪዎች እና የሚዛን አገልግሎት በሁሉም መናኸሪያዎች መሟላት ያለባቸው ቢሆንም በአዲስ አበባ አገር አቋራጭና የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና ሻሸመኔ ከተማ ባሉ መናኸሪያዎች ውስጥ ተሳፋሪዎች ወደ መናኸሪያ ሲገቡ ስለአገልግሎት አሰጣጡ መረጃ የሚያገኙበት ሁኔታ አለመኖሩና ከአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ አውቶብስ ተራ መናኸሪያ በስተቀር በሌሎች ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች የተዘጋጀ የተለየ መግቢያ በር አለመኖር፤ ሸኚ በማይገባባቸው መናኸሪያዎች ደግሞ ደንበኞች ዕቃቸውን የሚገፉበት ጋሪ አለመኖሩና በአስኮና ቃሊቲ መናኸሪያ ግቢ ውስጥ መብራት ባለመኖሩ መንገደኞች ለስርቆት አደጋ የሚጋለጡበት ሁኔታ መኖሩ፤

100. ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባው የፍጥነት ወሰን ሊኖረው እና ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን የካቲት 15/1961 ዓ.ም በደንብ ቁጥር 361/1961 የወጣ ቢሆንም 45 ዓመት የሆነው በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ እና ወቅታዊ መሻሻል ያልተደረገበት መሆኑ፤

የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

101. በጥቅል መገዛት ያለባቸውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን በቅድሚያ በመለየት በጥቅል እንዲከናወን መደረግ ሲገባው በናሙና በታዩት የድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ በከሰም ግድብና መስኖ ልማት እንደዚሁም በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከሲሚንቶ፣ ብረትና ነዳጅ በስተቀር ሌሎች በርካታ ለኮንስትራክሽን የሚያገለግሉ እቃዎች በጥቅል የማይገዙ መሆኑና

102. የድርጅቱ ንብረቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወጪ ከተደረጉ በኋላ በትክክል ለታቀደው ዓላማ የዋሉ ስለመሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ነገር ግን በተንዳሆና በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ሲሚንቶዎች፣ ብረቶች እና ለሎች የግንባታ እቃዎች ከንብረት ክፍል በአንድ ፎርማን በጥቅል ወጪ ከተደረጉ በኋላ ሳይት ላይ ላሉት ለሌሎች ፎርማኖች የጠየቁትን ያህል ያለምንም መተማመኛ/ሰነድ/ የሚታደል ሲሆን ለፎርማኖች ስንት እንደታደለ እና ስንት እንደቀረ የማይታወቅ መሆኑ፣ ከመጋዘን በጥቅል ወጪ የተደረገው የሲሚንቶ፣ ብረት እና ለሎች የግንባታ እቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ በትክክል የዋሉ ስለመሆኑ የሚታወቅበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፤

103. የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ብልሽት ሲገጥማቸው የብልሽቱ መንስኤ እየተጣራ አስፈላጊው ጥገና በወቅቱ ተደርጎላቸው በሥራ ላይ እንዲሰማሩ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለጥገና ጋራዥ ገብተው በወቅቱ ተጠግነው ያልወጡ እና ከአራት ወራት በላይ የሆናቸው በቃሊቲ ጋራዥ 383፣ በተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጄክት በተለያዩ ካምፖች በሚገኙ ጋራዦች 51 እና በከሰም ግድብ እና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተለያዩ ካምፖች በሚገኙ ጋራዦች 35 በጠቅላላው 469 የሆኑ የድርጅቱ ዶዘሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ግሬደሮች፣ ሎደሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ኮምፓክተሮች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች እና የተለያዩ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች መኖራቸውና በሌላ በኩል ድርጅቱ ለኪራይ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች በ2003፣ 2004 እና 2005 በጀት ዓመት ብር 174,500,362.35፣ ብር 432,349,783.00 እና ብር 697,594,994.21 እንደቅደም ተከተሉ ለኪራይ ወጪ ማድረጉ፤

104. ድርጅቱ ተሸከርካሪዎችንና ማሽነሪዎችን በኪራይ ከመጠቀሙ በፊት አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ ሊሰራ፤ ከኪራዩም ተገቢው አገልግሎት ስለመገኘቱ ሥራው በሚመለከታቸው የቅርብ ኃላፊዎች ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር እየተደረገ በየወሩ ለዋና መ/ቤት ሪፖርት ሊቀርብ የሚገባ ቢሆንም በተንዳሆ እና ከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በኪራይ የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች እና ተሸከርካሪዎች የሰሩበት ሰዓት ምዝገባ የሚከናወነው በሳይት ላይ በሚገኝ የቀን ሰራተኛ ሲሆን የኪራይ ገልባጭ መኪናዎች ምልልስ እና መሳሪያዎች የሰሩበት ሰዓት በብጣሽ ወረቀት ላይ የሚመዘገብ በመሆኑ፤ የኪራይ መሳሪያዎች እና ተሸከርካሪዎች ላልሰሩበት 2437.33 ሰዓት በአማካይ በተወሰደ የክፍያ ስሌት መሰረት ብር 4,387,194.00 ክፍያ አለአግባብ እንደተፈጸመ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የኪራይ ማሽነሪዎች ክፍያ ሰነድ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፤

105. አገልግሎት የማይሰጡ የድርጅቱ ንብረቶች፣ ተሸከርካሪ መኪናዎች፣ መሳሪያዎች፣ መለዋወጫ እቃዎች እና ኬሚካሎች በአግባቡ ሊቀመጡ እና በድርጅቱ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡ በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከአገልግሎት የተመለሱ ንብረት ክፍል ተመላሽ መደረግ የነበረባቸው የተለያዩ ውፍረት ያላቸው በርካታ ፌሮ ብረቶች እንደዚሁም 185 ዶዘሮች፣ ግሬደሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ኮምፓክተሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች፣ ለግንባታ ስራ የሚያገለግሉ የተለያዩ መሳሪያዎች እና ተሸከርካሪዎች በቃሊቲ ግቢ ውስጥ ሣይጠገኑ ወይም ሥራ ላይ ሣይውሉ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

በግል ጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

106. ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በሰውና በእንስሳት ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም ባሥልጣን መ/ቤቱ፤ የግል የጤና ተቋማትን የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ለመቆጣጠር በ2003 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም በእቅዱ አለማካተቱ፤ በዕቅዳቸው ውስጥ ያካተቱት የአዲስ አበባ አስተዳደር፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንደዚሁም የኦሮሚያ ጤና ቢሮዎችም በዕቅዱ መሰረት ቁጥጥር አለመድረጋቸው፤

107. ከጤና ተቋሞች የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተዘጋጀ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ቢኖርም በናሙና ተመርጠው በታዩት በአዲስ አበባ፣ በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልሎች በሚገኙ 42 የግል የጤና ተቋማት በሙሉ መመሪያው ያልደረሳቸው መሆኑ፤

108. በግል የጤና ተቋማት የጤና አገልግሎት ከሚሰጥባቸው ክፍሎች የሚወጡ ቆሻሻዎች ማጠራቀሚያና ማቃጠያ /ኢንስሌሬተር/ በሁሉም የጤና ተቋማት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መሰራትና አገልግሎት መስጠት ያለባቸው ቢሆንም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት የግል ጤና ተቋማት ውስጥ የተሰሩት የቆሻሻ ማጠራቀሚያና ማቃጠያዎች ወጥነት የሌላቸው አንዳንዶቹ ትልቅ አንዳንዶቹ ደግሞ ትንሽ ሲሆኑ፣ በራቸው ጠባብ እና ቆሻሻን ለመገልበጥ የማይመቹ፣ እንደዚሁም በሌሎች በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ የግል የጤና ተቋማት የሚሰሩ የቆሻሻ ማቃጠያዎች አገልግሎት የሰጡ መርፌዎችን ለማቃጠል የሚበቃ ሙቀት/ኃይል/ ያላቸው ባለመሆናቸው አገልግሎት የሰጡ መርፌዎች በደንብ ሳይቃጠሉና ወደ አመድነት ሳይቀየሩ የሚቀሩ ከመሆኑ በተጨማሪ አመዱ ከሌሎች ቆሻሻዎች ጋር ተወስዶ በከተሞች የቆሻሻ ማጠራቀሚያ የሚደፋ መሆኑ፤

109. ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ስለታማ እና ጫፋቸው ሹል የሆኑ የህክምና ቁሶች በተገቢው ሙቀት ሊቃጠሉ፣ ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ፍሳሾች ህብረተሰቡ ወደሚጠቀምባቸው ስፍራዎች ከመለቀቃቸው በፊት ሊታከሙ ሲገባ፣ የግል የጤና ተቋሞች በውሃ እና ፍሳሽ ቢሮ በላቦራቶሪ የጉዳት መጠናቸው ከመመርመሩ በፊት ህብረተሰቡ በሚጠቀምባቸው አካባቢዎች ለምሳሌ በወንዞች እና በፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች፣ በግለሰቦችና በተለያዩ ዘዴ የሚያስወግዱ መሆኑ፤

<u>በጂአይዜድ የተከናወኑ የጤና ተቋማት ግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

110. ጂ.ቲ.ዜድ እያንዳንዱን የጤና ጣቢያ ግንባታ ለሥራ ተቋራጮች በጨረታ አወዳድሮ መስጠት ቢኖርበትም ከተከናወኑት 475 የጤና ጣቢያዎች ግንባታ ፕሮጀክት 51% የሚሆኑት ለሥራ ተቋራጮች የተሰጡት ያለውድድር እና ያለ

ጨረታ መሆኑና ለአንድ ኮንትራክተር ከሁለት እስከ ሰባት የጤና ጣቢያ መሰጠቱ፤

111. በጂ.ቲ.ዜድ የተከናወነ እያንዳንዱ የጤና ተቋም ግንባታ በጂ.ቲ.ዜድ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተደረገው የውል ስምምነት መሠረት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ቢኖርበትም፤ በትግራይ ክልል አዲግራት ጤና ጣቢያ 1,332 ቀናት፣ በሱማሌ ክልል ለፊሳ ጤና ጣቢያ 1,193 ቀናት፣ በአማራ ክልል የመንጉዘር ጤና ጣቢያ 983 ቀናት፣ በኦሮሚያ ክልል የቦንዳዎ ጤና ጣቢያ 982 ቀናት እና በደቡብ ክልል ዳራዲሜ ጤና ጣቢያ 955 ቀናት የዘገዩ ሲሆን በጂ.ቲ.ዜድ በተገነቡ የጤና ተቋማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ሥራ በተያዘለት ጊዜ ባለመጀመሩ በኦሮሚያ ከተገነቡት 169 ጤና ጣቢያዎች 113ቱ የዘገዩ መሆኑ፤

112. በጂ.ቲ.ዜድ ከተከናወኑ የጤና ተቋማት ውስጥ የግንባታ የጥራት ችግር ባለባቸው ላይ እና በተለያዩ ምክንያቶች በአፋር፣ በትግራይ፣ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ደቡብ ሕ/ብ/ብ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ ክልሎች በአጠቃላይ 158 ጤና ጣቢያዎች ላይ (የተጨማሪ ስራዎችን ሳይጨምር) በውለታው መሠረት በአንድ ዓመት የመታያ ጊዜ ውስጥ (Warranty period) ሥራው ባለመጠናቀቁ የመጨረሻው ርክክብ አለመፈጸሙ፤

113. የግንባታ ጥሬ ዕቃ ዋጋ ንረት በመከሰቱ ፣ በጀት በሚያዝበት ወቅት ከግምት ውስጥ መግባት የነበረባቸው ጤና ጣቢያዎቹ የሚገኝበት የአፈር አይነት፣ ሳይቱ የሚገኝበት ርቀት፣ እና ሌሎች ምክንያቶች ከግምት ውስጥ ባለመግባታቸው የ144 ጤና ጣቢያዎች ግንባታ በተያዘለት በጀት መጠናቀቅ አለመቻሉ፤ በአጠቃላይ በሁሉም ክልሎች ለተገነቡ ጤና ጣቢያዎች ከተያዘላቸው ዋጋ በላይ ብር 105,270,698.97 ወጪ የተደረገ መሆኑ፤

114. በአጠቃላይ በጂ.ቲ.ዜድ ከተገነቡ 475 ጤና ጣቢያዎች ውስጥ በኦሮሚያ 26፣ በአማራ 28፣ በደቡብ 22፣ በትግራይ 10፣ በአፋር 6፣ በሱማሌ 1፣ በቤኒሻንጉል 10፣ እና በጋምቤላ 1 በድምሩ በ104 ጤና ጣቢያዎች ላይ የጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑ፤ በመስክ ጉብኝት ወቅት እነደታየው የጥራት ችግር ካለባቸው መካከል አማላማ እና አዋሽ ቡኔ የጤና ጣቢያዎች ችግሮች በቀላል ጥገና ሊስተካከሉ የማይችሉ መሆናቸው፤

<u>በስኳር ኮርፖሬሽን የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች አፈጻምን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

115. በኮርፖሬሽኑ የአምስት ዓመታት ዕቅድ (2003-2007 ዓ.ም) መሠረት አዲስ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶች የአገዳ ተክል ልማት ዕቅድ ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም በጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክት 18,400 ሄክታር ሲሆን ክንውን 2,395 ሄክታር (13%)፤ በኦሞ ኩራዝ ዕቅድ 43,108 ሄክታር ሲሆን ክንውን 1,676.6 ሄክታር (4%) እና በወልቃይት እቅድ 8,608 ሄክታር ሲሆን ክንውን 539 ሄክታር (6.5%) መሆኑ፤

116. በአምስት ዓመታቱ የፋብሪካዎች ግንባታ ዕቅድ መሠረት (ከ2003 - 2005 ዓ.ም) የጣና በለስ ቁጥር አንድ እና ሁለት እስከ ጥቅምት 2005 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲኖርበት ክንውኑ በ2005 ዓ.ም መጨረሻ ቁጥር አንድ 45% እና ቁጥር ሁለት 39% መሆኑ፣ በኦሞ-ኩራዝ የፋብሪካ ግንባታው እስከ ሰኔ 2005 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲኖርበት ክንውን 42% መሆኑ፤ ወልቃይት እስከ ጥቅምት 2006 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲኖርበት ሥራው ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለመጀመሩ፤

117. የስኳር ልማት ፕሮጀክት አካል የሆኑት የመስኖ ልማት፣ የአገዳ ተክል እና የፋብሪካ ግንባታ ስራዎችን ሥራዎችን በቅንጅት ባለመታቀዳቸውና አፈጻጸሙ ቅደም ተከተል ጠብቆ ባለመተግበሩ የአንዱ አፈጻጸም መዘግየት በሌላው ሥራ አፈጻጸም ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ፤

118. ለአብነት የተንዳሆ ስኳር ልማት የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት በታቀደለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ ምክንያት 5164.09 ሄክታር መሬት ላይ የለማ የሸንኮራ አገዳ ምርት ዕድሜው በመራዘሙ እንዲወገድ በመደረጉ 102,440,145.00 ብር ፋብሪካው ማግኘት የሚገባውን ገቢ ተገቢ ባልሆነ መልኩ ያሳጣ መሆኑ፤

119. የአገዳ ተክል ልማት፤ የመስኖ ግንባታ እና የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶች በየደረጃው የተሰሩ ስራዎች በተቀመጠለት ዲዛይን እና እስፔሲፊኬሽን መሰረት መሆኑ በተቆጣጣሪ መሃንዲሱ ሊረጋገጥ የሚገባ ቢሆንም ኮርፖሬሽኑ ሊያስገነባቸው ላቀደላቸው አስር አዳዲስ የስኳር ፋብሪካ ግንባታዎች ሥራቸው በተጀመረበት ወቅት ጥራት የሚቆጣጠር አማካሪ ድርጅት ባለመቅጠሩ የጣና በለስና ኩራዝ ፋብሪካ ግንባታ (ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ከ2003 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ

ጥቅምት 2006) በየደረጃው እየተከናወኑ የነበሩ ሥራዎች (civil work) በተቀመጠለት ዲዛይንና እስፔሲፊኬሽን መሰረት ስለመሆኑ በተቆጣጣሪ መሃንዲስ አለመረጋገጡ፤

120. ለጣና በለስ ቁጥር 1፣ ቁጥር 2 እና ለኦሞ ኩራዝ ቁጥር 1 የፋብሪካ ግንባታ ስራቸው የተጀመረው መጋቢት 2003 ዓ.ም ሲሆን ኮርፖሬሽኑ አማካሪ ድርጅት የቀጠረው ሥራው ከተጀመረ ከሁለት ዓመት በኋላ ሐምሌ 10 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑ፤

<u>በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የካሳ ክፍያ አከፋፈልን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

121. አዋጅ ቁጥር 455/1997ን ለማስፈጸም ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ስለሚከፈል ካሳ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ቁጥር 135/1999ን መሠረት በማድረግ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያ የአተማመን ቀመር ሊዘጋጅና ወቅታዊ ሊያደረግ ሲገባ አለመዘጋጀቱ

122. ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚነሱ ባለይዞታዎች የሚከፈለው የካሳ ግምት በበቂ መረጃ ላይ የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡ የካሳ ክፍያ ግምት ከመሰራቱ በፊት የፕሮጀክቱ አዋጭነት ጥናትና የሚያርፍባቸው ቦታዎች መልሶ ማቋቋሚያ መርሀ ግብር (Resettelement action plan) ሲጠናም ሆነ የካሳ ገማች ኮሚቴው በልማት የሚነሱ ንብረቶችን የግምት ሥራውን ሲሰራ በበቂ መረጃ ላይ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከተከለሱ ከካሳ ክፍያ ጋር የተያያዙ አላማጣ- መሆኒ- መቀሌ እና ቆቃ -ሁርሶ- ድሬዳዋ የ230 ኪ.ቮ. የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ፕሮጀክቶችና፣ የአሉቶ- ላንጋኖ ፕሮጀክት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚወጣውን ስታትስቲካዊ መረጃ አለመጠቀማቸው፤ የኮርፖሬሽኑ የአዋጭነት ጥናት እና የገማች ኮሚቴ የካሳ ግምትም አንድ አለመሆኑ፤

123. ለልማት አገልግሎት እንዲለቀቅ በተወሰነ መሬትና በመሬቱ ላይ የሚገኙ ንብረቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት የከተማው ወይንም የወረዳው አስተዳደር ሊይዝ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህርዳር ከተማ መስተዳደር፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን የባህርዳር ዙሪያና የይልማና ዴንሳ

ወረዳዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በጉራጌ ዞን የመስቃን ወረዳ፣ በሀዲያ ዞን የሌሞ ወረዳ ለኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ማስተላለፊያ ሥራ ለማከናወን የተነሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ የተጠናቀሩ መረጃዎች በከተማው ወይንም በወረዳው አስተዳደር ያልተያዙ መሆኑ ታውቋል፡፡

124. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር የሚኖርበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው የባህር ዳር-ደብረ-ማርቆስ-አዲስ አባባ፤ ወላይታ ሶዶ -አዲስ አበባ 400 ኪሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክቶች የክልል መስተዳደር ጽ/ቤቶች፣ የከተማና የወረዳ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እንደዚሁም የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴዎችም ሆነ ከካሳ ከፋዮች (ኮርፖሬሽኑም) ጋር ካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ከክልሎችና ከልማት ፈጻሚ አካላት ጋር የምክክር መድረክ የሌላቸው መሆኑ፤

<u>በኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት የእህል ግዥ፣ ሽያጭ እና ክምችትን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

125. የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እህል ሲገዙም ሆነ ሲያከማቹ ድርጅቱ ባስቀመጠው የጥራት ደረጃ መመሪያ መሰረት ሊሆን ሲገባ በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 3 ቅርንጫፎች በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥር የሚገኙ የእህል መጋዘኖች የእህል አደራደር የተዝረከረከ እና የተዘበራረቀ መሆኑ፤ በመጋዘኖቹ ወስጥ እህል ከመቋጠሪያ ዉጪ ፈሶ መታየቱ፣ በመጋዘኖቹ ውስጥ ባዶ የእህል መቋጠሪያ ጆንያዎች በብዛት ተከማችተው እና ተዝረክርከው መገኘታቸው፣ የድንገተኛ የእሳት ቃጠሎን ለመከላከል የሚያስችል የእሳት ማጥፊያ መሣሪዎች አለመኖሩ፣ በየመጋዘኖቹ የእህል ማስቀመጫ ፓኔሎች የሌሉ በመሆኑ እህል መሬት ላይ እንዲቀመጥ መደረጉ፣ በመጋዘን ቁጥር 11 ግቢ ውስጥ የግለሰቦች መኖሪያዎች ያሉበት መሆኑ፣ አእዋፋት ወደመጋዘኑ የሚገቡበት ሁኔታ መኖር፤ በአሰላ እና በባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መጋዘን ውስጥ ለእህል ህክምና አገልግሎት የሚውሉ መድኃኒቶች አያያዝ የተዝረከረከ እና መድኃኒቶቹ በሰው እና በአካባቢ ላይ አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉበት

ሁኔታ ተቀምጠው መገኘታቸውና አገልግሎት የማይሰጡ እና የተበላሹ ብዛት ያላቸው የእህል ማበጠሪያ ማሽኖች በየመጋዘኖቹ ተተክለው የሚገኙ መሆኑ፣

<u>በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚመነጩ የተለያዩ ቆሻሻዎችን ለመያዝ፣ ለማጓጓዝና ለማስወገድ የሚረዳ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱና እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ የተካሄደ ክዋኔ ኦዲት፤</u>

126. ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ጉዳት እንዳያመጣ ለማምከንና ለማስወገድ የሚያስችለውን የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸውን ደረቅ፣ ፈሳሽና አደገኛ ቆሻሻዎች ለመሰብሰብ፣ ለማጓጓዝ፣ እንደ አግባብነቱ ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማስወገድ የሚያስችለውን ወጥ የሆነ የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝ የአሰራር ስርአት አለመዘርጋቱ፡፡

127. ዩኒቨርሲቲው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ፣ በአመት ምን ያህል ቆሻሻ ከዩኒቨርሲቲው እንደሚያመነጭ እና በምን አይነት መንገድ መሰብሰብ፣ መያዝ፣ መጓጓዝና መወገድ እንዳለበት የሚያሳይ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ሲገባ ዩኒቨርሲቲው ዕቅድ ያላዘጋጀና ተግባራዊ ያላደረገ ነገር ግን ስራው በተለምዶ የሚከናወን መሆኑ፤

128. ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማለትም እንደ ቆሻሻው አይነት እና ባህሪ በመለየት የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣ የማጓጓዝና የማስወገድ ስራን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲኖርና ስራው እንዲከናወን ሊያደርግ ቢገባም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት፣ የጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ አራት ኪሎ ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንሲቲትዩት፣ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ፣ የንግድ ስራ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢኒስቲትዩት፣ አቃቂ የሀገር ልማት እና ደብረ-ዘይት የእንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ ደረቅ፣ ፈሳሽና አደገኛ ቆሻሻዎችን በአይነት እንዲሁም በባህሪ አደገኛ የሆኑትን በመለየት የማያስወግዱ መሆናቸው፤

129. ዩኒቨርሲቲው ከማስተማሪያ የምርምር ቤተ-ሙከራዎችና ከክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ፍሳሽ እና ሌሎች ቆሻሻዎች ከመወገዳቸው በፊት በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ተገቢው ጥንቃቄ ሊያደረግ የሚገባ ቢሆንም ከዩኒቨርሲቲው

የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የተፈጥሮ ሳይንስና ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የምርምር ቤተ ሙከራዎች እና ክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች ጉዳት የማያስከትሉ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ወደ ፍሳሽ ቱቦዎች የሚለቀቁ መሆኑ፣

130. ከዩኒቨርሲቲው ጤና ተቋማት የሚመነጩ ሌሎች አደገኛ እና ስለታም ቆሻሻዎች ተለይተው የሚሰበሰቡና የሚከማቹ ቢሆንም፣ በየቀኑ ጉዳት እንዳያሰከትሉ ጥንቃቄ በማድረግ የማጓጓዝና የማስወገድ ተግባር የማይከናወንና ከሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች ጋር አብሮ የሚወገድ መሆኑ፤

የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችትና ሥርጭት አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት፤

131. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሚከናወነው ዓመታዊ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዲሆን በፍላጎት ጥናት ላይ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት መሥራት የሚጠበቅበት ቢሆንም በናሙና በታዩት በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ ሽያጭና ሥርጭት ጣቢያዎች አርሶ አደሮች፣ ኢንቬስተሮች፣ የእርሻ ልማቶች ወ.ዘ.ተ የሚፈልጉትን የምርት ማሳደጊያዎች መጠን ያሳወቁበት (ፍላጎት የተሰበሰበበት) መረጃ ተጠናቅሮ ሳይያዝ ካለፈው አመት የግብዓት ፍላጎት መጠን በመነሳት ግዥ የሚፈጽሙ መሆኑ፤

132. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ከክብደት በታች (Under Weight) የግብርና ግብዓት ከወደብ ወደ መሀል አገር እንዳይጓጓዝ በተለይም ተጠቃሚው ወደ ሆነው አርሶ አደር በቀጥታ እንዳይደርስ እንዲሁም ሾፌሩ ጭነት በጫነበትና ዕቃውን ወይም ጭነቱን ባስረከበበት ሰነዶች መካከል የባከነ ንብረት ወይም ልዩነት እንዳይኖር ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጋቸው በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው በናሙና በታዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት እና መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ከክብደት በታች (Under Weight) 50 ኪ.ግ. መሆን ሲገባቸው የማዳበሪያው ከረጢት ሳይፈታ ከ44- 49 ኪ.ግ. የሆኑ የምርት ማሳደጊያዎች ለአርሶ አደሮች የሚደርሱ መሆኑ፤ በመጋዘን ውስጥ ለሚከሰቱ የግብዓቶች ፍሳሽ (ጉድለት) መጠን

በየአመቱ ተጠናቅሮ በመረጃነት አለመያዙ፤ እንዲሁም ከክብደት በታች የሆኑ ማዳበሪያዎች ክትትል እየተደረገባቸው ወዲያውኑ ለሌላ ብክነት ሳይጋለጡ ሪባግ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

133. በማንኛውም ምክንያት በማዕከል እና በሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት መጋዘኖች ሊወገዱ የሚገባቸው፣ ለተጠቃሚ ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የግብርና ግብአቶች ዝርዝር ሊያዝና ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚገባ ቢሆንም በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል በሚገኙ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት እና በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት መጋዘኖች የሚወገዱ፣ ለተጠቃሚው ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የግብርና ግብዓቶች ዝርዝር መረጃ ተጠናቅሮ እንዲያዝ እና ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ እንዲሰጥበት አለመደረጉ፤

134. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች የሥርጭት ፕሮግራም ሊዘጋጅ በተዘጋጀውም የሥርጭት ፕሮግራም መሠረትና ተጠቃሚዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ በመመርኮዝ የግብርና ግብዓት ሥርጭት ሊፈጸም፣ የሚያጓጉዘበትን የሥርጭት ጊዜ፣ መጠንና የጣቢያዎችን ዝርዝር የያዘ የስርጭት ፕሮግራም ተጠናቅሮ ሊያዝ እና ሥምሪት የወሰደው ሾፌርም በተሰጠው ስምሪት መሰረት ከመነሻው እስከ መድረሻ ይፈጃል ተብሎ በተወሰነው የጉዞ ሰሌዳ መሰረት መድረሱን እና የባከነ ጊዜ አለመኖሩ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

135. በናሙና በታዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት፣ በኦሮሚያ እና አማራ ክልል የሚገኙ ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት የሥርጭት ጊዜና መጠን የያዘ የሥርጭት ፕሮግራም እንደማያዘጋጁ እና መረጃዎቹንም አጠናቅረው የማይዙ መሆኑ፣

<u>በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የታክስ ኦዲት ተግባር አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት</u>

136. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ የታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂውን መሰረት ያደረገ አንድ ወጥ ተቋማዊ ዕቅድ አሳታፊ በሆነ

መንገድ አዘጋጅቶ ለሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ያደረገ ቢሆንም፣ ቅ/ጽ/ቤቶች የተዘጋጀውን ተቋማዊ የኦዲት ስራ ዕቅድ መሰረት በማድረግ የተሟለ ዝርዝር የኦዲት ዕቅድ አዘጋጅተው ተግባራዊ የማያደርጉ መሆኑ፤

137. የግብር ከፋዮች ደረጃን፣ የኦዲት አይነት እንዲሁም የንግዱን እንቅስቃሴ መሰረት ያደረገ የኦዲት የጊዜ ስታንደርድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ፤ ለኦዲት የተመሩ የግብር ከፋይ ፋይሎች ኦዲት በተቀመጠው የጊዜ ዕቅድ መሠረት ሊከናወን፤ እያንዳንዱ ኦዲትም በተቀመጠው የኦዲት ጊዜ ተመን ውስጥ ስለመከናወኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

138. በኦዲቱ ወቅት በባለስልጣን መ/ቤቱ ለእያንዳንዱ የኦዲት አይነት እንዲሁም በየቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ ግብር ከፋዮችን ደረጃ በመለየት ስታንደርድ ያዘጋጀ ቢሆንም በናሙና በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች እያንዳንዱ ኦዲት በታቀደለት ወቅት እና የጊዜ ተመን የሚከናወን ሰለመሆኑ የሚደረግ ክትትልና የተወሰደ እርምጃን የሚያሣይ መረጃ አለመገኘቱ፣

139. የግብርና ታክስ ኦዲት ስራዎችን ተገቢና ምቹ በሆነ መልክ ለማደራጀት፣ ለመመደብና ለመገምገም እንዲሁም ግብር ከፋዩን በእኩልነትና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለታክስ ኦዲት ለመምረጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንደዚሁም የተዘረገው የአሰራር ስርዓት በአግባቡና ወጥ በሆነ መልኩ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ስለመደረጉ በዋና መ/ቤት ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ሲገባ በተሟላ መንገድ የማይፈጸም መሆኑ፤

140. የኦዲት ስራ አፈፃፀም ደረጃውን የጠበቀና የንግዱን እንቅስቃሴ ተከትሎ ክህሎቱ ባላቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን ለማድረግ የሚያስችል ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ/ ለኦዲተሮች የሚመሩበት ወጥ የሆነ መስፈርት በተቋም ደረጃ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶችም በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት የግብር ከፋይ ማህደራትን ለኦዲተሮች ሊመሩ ይገባል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶች በመስፈርቱ መሰረት ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

141. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ለታክስ ኦዲት የተመረጡ የግብር ከፋይ ማህደራት በስራ ሂደቱ ስር ለሚገኙ የቡድን አስተባባሪዎች እንዲሁም የቡድን አስተባባሪዎችም በተዋረድ በስራቸው ለሚገኙ ለእያንዳንዱ ኦዲተር(ኦዲተሮች) የሚደለደልበት ወይም የሚከፋፍልበት የስራውን ውስብስብነት፣ ግብር ከፋዩ የተሰማራበትን ዘርፍ፣ የቡድኑን ወይም የኦዲተሩን እውቀትና ክህሎት ወ.ዘ.ተ መሰረት ያደረገ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው ወጥ የሆነ መስፈርት የሌለው መሆኑ፤

142. እያንዳንዱ ኦዲት ሲካሄድ መከተል ያለበት አሰራሮች በኦዲት ስራ ወረቀቶች የተደገፉ እንዲሁም በኦዲተሮች የተዘጋጁት መግለጫዎችና ሌሎች ሰነዶች ተፈርመው ከኦዲት ውጤቱ ማጠቃለያ ጋር ለስራ ሂደቱ ሊቀርቡ፤ የኦዲት ስራ ወረቀቶቹም ባግባቡ ሊደራጁ (ግልፅ እና የተሟሉ) እና በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ በሚያስችሉ መልኩ በህግ ለተወሰነው የጊዜ ገደብ በአግባቡ ሊጠበቁ በሚችሉበት ቦታ እንዲቀመጡ ሊደረጉ የሚገባ ቢሆንም በአንጻራዊ መልኩ ከከፍተኛ ግብር ከፋዮች በስተቀር በሌሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተሟላ ሆኔታ መረጃዎቹ የማይያዙ መሆኑ፤

143. በታክስ ኦዲት ወቅት በግብር ከፋዩ ከሚቀርበው መረጃ በተጨማሪ የሶስተኛ ወገን፣ የዊዝሆልዲንግ እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚገኙ መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት እንዲደረጉ ለተመረጡ ለሁሉም የግብር ከፋይ ማህደራት ለኦዲት ስራው የሚያገለግሉ እነኚህ ተጨማሪ መረጃዎች ኦዲቱ ከመጀመሩ በፊት አስቀድመው ተጠናቅረው የማይያዙ ወይም የማይሰበሰቡ ከመሆኑም በላይ በኦዲት ወቅትም በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ የማይውሉ መሆኑ፤

144. በተገኙ የኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው ዕርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ተገቢው እርምጃም ስለመወሰዱ በየደረጃው (በዋና መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች) ተገቢው ክትትል ተደርጎ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

145. በዚሁ መሠረት በናሙና በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች በተደረጉ የተለያዩ የኦዲት አይነቶችን በማከናወን ለአብነትም በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከ2002 እስከ 2005 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወር ድረስ ብር 2,025,438,108.21 ተጨማሪ ፍሬ ግብር/ታክስ እና ብር 2,923,323,143.86 ወለድና መቀጫ በድምሩ ብር 4,948,761,252.07 የተወሰነ መሆኑ፡

146. ነገር ግን በ2002 በጀት ዓመት 378 የሚሆኑ ግብር ከፋዩች ባቀረቡት የመቀጫ ይነሳልኝ አቤቱታ መሰረት ከተጣለው የመቀጫ መጠን ብር 54,411,310.83 ውስጥ ብር 45,104,015.21 (83 በመቶ) ቀሪ በማድረግ ብር 9,307,295.62 (17 በመቶ) ብቻ እንዲከፍሉ የፀና መሆኑን፣ በ2003 በጀት ዓመት ደግሞ የ1052 የሚሆኑ ግብር ከፋዩች ላይ ከተጣለው መቀጫ መጠን ብር 103,514,519.8 ውስጥ ብር 84,488,177.73 (82 በመቶ) ቀሪ በማድረግ ብር 19,026,342.7 (18 በመቶ) ብቻ እንዲከፍሉ የፀና መሆኑ፤

<u>በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ፤ አሻሻጥ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ ክትትልና አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት</u>

147. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ የግብርና ምርቶችን አሠባሠብ አያያዝና በመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታን አስመልክቶ ተገቢውን ጥናት በማካሄድ በቅድሚያ ሊያውቅ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል በ 2005 ዓ.ም በመጋቢት ወር ገበያ ለመቅረብ የደረሰ የሽንኩርት ማሳ መነቀል የነበረበት ከ 1 ወር በፊት ቢሆንም፣ በወቅቱ ባለመነቀሉ 250 ኩንታል የሚሆን ሽንኩርት በማሳው ላይ እያለ መበላሸቱ፤

148. በሸዋ ሮቢት ማረሚያ ቤት የግብርና ምርቶች ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ከሶስት አመት በፊት ጊዜው ያለፈበት አደገኛ ኬሚካል (Bayleton 25 WP) ከተለያዩ ምርቶች (ቲማቲም፤ ማንጎ፤ በቆሎ.....ከመሳሰሉት) ጋር መቀመጡና በምርቱ ላይ እና በመጋዘኑ ሰራተኞች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል፤ ኬሚካሉ እንዲወገድላቸው የመጋዘኑ ሠራተኞች ለማረሚያ ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቃል በተደጋጋሚ እንደጠየቁና መልስ ማጣታቸውን፤ በቃለ መጠይቅ ወቅት የገለጹ ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅትም ችግሩ አለመፈታቱን በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

149. የምርት ማቅረቢያ ማዘዣ ምርት ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት፤ ደረጃ፤ መጠን፤ የአቅርቦት እለትና ሰዓት፤ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ/ካርድ

ማዕከላት ሊጠቀሙ ቢገባም በናሙና በተመረጡ ማዕከላት ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት፣ ደረጃ፣ መጠን፣ የአቅርቦት እለትና ሰዓት፣ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ/ካርድ የሚጠቀሙበት የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑ፣

150. ማዕከላት የሚሸጡትን ምርቶች አይነትና የሽያጭ ፕሮግራም ለደንበኞች በግልጽ በሚታይ ቦታ ማስታወቂያ መለጠፍና እንደአስፈላጊነቱ በሚዲያ ሊያስነግሩ የሚገባ ቢሆንም በናሙና በተመረጡ ማዕከላት ለደንበኞች ምርቱን ለመሸጥ የማስተዋወቅ ስራ አለመሰራታቸው እና የምርት አሻሻጥ፣ ተግባራትና ዘዴዎቹ ግልጽ አለመሆናቸው፣

151. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ወቅታዊ የሆነና የተደራጀ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ መመሪያ ሊያዘጋጅና ለሚመለከታቸው ማዕከላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በመመሪያው ዓላማ መሠረት ማዕከላቶች ትርፋማና በገበያ ተወዳዳሪ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለግብርና ምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ ተፈጻሚነቱ በአስተዳደሩ ስር ለሚገኙ ለዝዋይ፣ ለድሬዳዋ እና ለሸዋ ሮቢት ማረሚያ ቤቶች እንዲውል መመሪያ አውጥቶ ለማዕከላቱ ቢያሰራጭም ተግባራዊ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ አለማደረጉ፣

152. የምርት ዋጋ ተማኝ፣ የምርት አስረካቢ እና የምርት አስወጋጅ ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በናሙና በተመረጡ ማዕከላት በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ፣

<u>በመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀምን በተመለከተ የተናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

153. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና ቁጥጥር ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያን ወጥ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት ወይም ተቋማቱ እንዲያዘጋጁ እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

154. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩት አራት የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች) የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያ ወጥ በሆነ መልኩ አለመዘጋጀቱ፤ ተቋማቱም እንዲያዘጋጁ እገዛ አለመደረጉ

155. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውስጥ ገቢ የበጀት ኮድ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ከተመደበላቸው በጀት በላይ ሊጠቀሙ አይገባም፤ እንዚሁም ገቢውን በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ከሚሰራው ሥራ ጋር በማጣጣም በየወሩ የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ እቅድ አዘጋጅተው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

156. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት አራት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) በሁሉም የተመደበላቸው በጀት ከአፈጻጸሙ ጋር የማይጣጣም ሲሆን፣ በየወሩም የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ የማያዘጋጁ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይህን ያህል በጀት ይጽደቅልኝ ብሎ ገ/ኢ/ል/ሚ/ርን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ከውስጥ ገቢ የተጠቀመውን መጠን ሙሉ በሙሉ የማያሳውቅ እና በሪፖርቱ ውስጥም የማያካትት መሆኑ፤

157. በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢን የሚሰበስቡ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ የታቀፉ፣ የአሰራር ሥርዓት ያላቸው በዚሁ ሥርዓት የሚመሩ መሆን አለባቸው፡፡

158. ይሁንና በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአዲስ አበባ፣ ባህር ዳር፣ አዳማ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢን የሚሰበስቡ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ የታቀፉ እና የአሰራር ሥርዓት ያላቸው ባለመሆናቸው ምክንያት ለግለሰብ ጭምር የገቢ ማመንጫ ተቋማቶቹን በነጻ የሚሰጡ ከመሆኑ በላይ የገቢ ማመንጫ የሥራ ሂደት እያንዳንዱ የገቢ ማመንጫ ያስገኘውን ገቢ ለይቶ አለማወቁ፤ እንዲሁም የገቢ ማመንጫዎቹ ውል ሰጪ በዩኒቨርሲቲዎቹ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መምሪያዎች /ሶሻል፣ ግዥ፣ ቤቶች ልማት፣ የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት/ መሆናቸው፤

159. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊያሳውቁ፣ ገቢና ወጪን ሊመዘግቡ እንዲሁም ኦዲት አስደርገው ለሚመለከተው የበላይ አካል ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

160. ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የማያሳውቁ ሲሆን ከውስጥ ገቢ የሰበሰቡትን እና ወጪ ያደረጉትን ሙሉ በሙሉ በበጀት ኮድ የማይመዘግቡ መሆኑ፣

የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያ እቃዎች ግዢና ስርጭት በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

161. የመድኃኒት ብክነት እና እጥረት እንዳይደርስ ለመከላከል የተጠናከረ፣ ተመጣጣኝና ተገቢ የመድኃኒት ክምችት፣ ያልተቋረጠ አቅርቦትና ስርጭት የሚኖርበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ አፈጻጸሙንም በተመለከተ ተገቢው የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ሊፈጸም ይገባል፡፡

162. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የመንግስት ሕክምና መስጫ ተቋማት የመድሃኒት አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ቢመጣም፣ አሁንም የአቅርቦት መቆራረጥና ክፍተት መኖሩ በተለይ የኬሚካሎችና ላብራቶሪ ሪኤጀንቶች (Chemicals and lab-reagents) አቅርቦት ከፍተኛ እጥረት መኖሩ፣ በተጨማሪም በናሙና በታዩት በሁሉም (17) ጤና ተቋማት ኤጀንሲው የተጠየቁትን መድሃኒቶች ሙሉ ለሙሉ ማቅረብ እንዳልቻለ የገለፁ ሲሆን፣ በፈለገ-ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል በ1/21/2006 ዓ.ም በተደረገ ጉብኝት አስፈላጊ ከሆኑት 42 አይነት መድሃኒቶች በሆስፒታሉ መድሃኒት ማከማቻ መጋዘን ምንም ክምችት አለመገኘቱ፣

163. ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ቁልፍ ባለው የብረት ሳጥን ውስጥ ወይም በተለየ ክፍል መቀመጥና ቁልፉም በተፈቀደለት ባለሙያ እጅ ብቻ መኖር የነበረበት ቢሆንም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩት 17 መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት መካከል በ15 ተቋማት የመድሃኒት መጋዘኖች ውስጥ ለናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች የተለየ ሳጥንም ሆነ የተለየ ባለሙያ አለመኖሩ፣

164. በማዕከልና በቅርንጫፍ መጋዘኖች እንዲሁም በመንግስታዊ የሕክምና መስጫ ጤና ተቋማት የሚኖረዉ የክምችት መጠን ከሚፈለገዉ በታች ወይም በላይ እንዳይሆን ወይም በአጠቃላይ ከክምችት ጠፍቶ ችግር እንዳይፈጠር የክምችት መጠን አመላካቾች (Average monthly consumption, Minimum stock level, safety stock Level) በየደረጃው (በማዕከልና በቅርንጫፍ መጋዘኖች እንዲሁም በጤና ተቋሞች) በሥራ ላይ ማዋል ያለባቸው ቢሆንም በናሙና ከታዩት መንግስታዊ ጤና ተቋማት መካከል በቦንጋ፣ በጋምቤላ፣ በኡኬ፣ በጢጣ እና በጉቴ ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም በጥቁር አንበሳና ጳውሎስ ሆስፒታሎች የመድሃኒት መጠን አመላካቾቹ ስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ፤

165. የሚወገዱትን መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ጥቅም ላይ የማይውሉበትን ምክንያትና መንስኤ በማወቅ ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ በኦዲቱ በታዩት አምስት የኤጀንሲው ቅርንጫፎችም ሆነ በ17 የመንግስት ጤና ተቋማት በስራቸው የሚወገዱትን መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ጥቅም ላይ የማይውሉበትን ምክንያትና መንስኤ ለማወቅ የተደረገ ጥናት አለመኖሩ፤

<u>በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

166. በተራዘመ ክፍያ የልማት ድርጅቶችን የገዙ ባለሀብቶች የሚፈለግባቸውን ቀሪ ሂሳብ በወቅቱ እንዲከፍሉ ኤጀንሲው አመታዊ የክፍያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ክፍያቸውን በገቡት ውል መሰረት እንዲፈጽሙ በደብዳቤ፣ ቦታው ድረስ ሄዶ በመነጋገርትና የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የክፍያ ጥያቄ የሚያቀርብና ክትትል የሚያደርግ መሆኑን ከሠነዶችና ለባለሀብቶች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት የተቻለ ቢሆንም ቅድሚያ ክፍያ ፈጽመው ውል ከገቡ በኋላ ቀሪ ክፍያቸውን በገቡት ውል መሰረት ያላጠናቀቁ ድርጅቶች ስለመኖራቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ እስከ ህዳር 30/2006 ዓ.ም. ድረስ መጠናቀቅ የነበረበት ከሃያ ዘጠኝ የልማት ድርጅቶች በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ እና ከሁለት እስከ አምስት አመት የዘገየ ሂሳብ ብር 362,394,242.11 (ሶስት መቶ ስድሳ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሁለት ብር ከአስራ አንድ ሳንቲም) እና 300,318.06 (ሶስት መቶ ሺህ ሶስት መቶ አስራ ስምንት ከዜሮ ስድስት ፓውንድ) ፓውንድ መኖሩ፤

167. ኤጀንሲው ከድርጅቶቹ የሚፈለገው ቀሪ እዳ ለማሰባሰብ ክትትል እያደረገ የሚገኝና በዚሁ መሰረት ከተጠቀሱት 30 ድርጅቶች ውስጥ 7ቱ በፍርድ ቤት በክስ ላይ የሚገኙና ወደአፈጻጸም የተሸጋገሩ 23ቱ ደግሞ የክስ ሂደታቸው ተጀምሮ በህግ የተያዘ መሆናቸውን የገለጠ ቢሆንም ከባለሀብቶቹ የሚፈለገው ቀሪ ሂሳብ ከፍተኛ በመሆኑ ኤጀንሲው አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ ቀሪ እዳው በአስቸኳይ እንዲሰበሰብ ማድረግ አለበት፡፡

በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም በተመለከተ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት

168. አገልግሎቱ ከ2003-2005 ባሉት ጊዜያት በመርሐ-ግብር የተደገፈ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ግገር ዕቅድ በማዘጋጀት ባለበጀት መ/ቤቶቹ በአገልግሎቱ በኩል የሚገዙትንና የማይገዙትን ዕቃዎች እና የአልግሎቱ ግዥ የሚፈፀመው መቼ እንደሆነ በጊዜ ባለማሳወቁ ባለበጀት መ/ቤቶች በራሳቸው የሚገዙትን ዕቃዎች አቅደው ግዥ በወቅቱ እንዳያከናወኑ ያደረገ መሆኑና በጀታቸውን በአግባቡ ከአገልግቱ ኘሮግራም ጋር አጣጥመው ለመጠቀም እንዳላስቻላቸው፣

169. በግዥና ውል አስተዳደር እና በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉና በኤጀንሲው የተወሰኑትን ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን /Common user items/ በተመለከተ የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት በየዓመቱ ከመጋቢት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ለቀጣይ በጀት ዓመት የሚገዙ ግዥዎችን ሊያሰባስብ እና በአስር የስራ ቀናት ውስጥ በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት ደረጃ እና በሚገኝበት ቦታ በተለያየ ምድብ /በሎት/ ሊለይ እንዲሁም ከገበያ ጥናት የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን ፍላጎት ማደራጀት ሲገባው፤ አልግሎቱ በ2003 ዓ.ም. ለ2004 በጀት ዓመት የፍላጎት ማሳወቂያ ደብዳቤውን የላከው ማሰባሰብ ካለበት 5 ወር ዘግይቶ መሆኑ፣ በ2004 ዓ.ም. ለ2005 በጀት ዓመት ማሰባሰብ ከነበረበት ጊዜ ከ2-8 ወራት ዘግይቶ የላከ በመሆኑ በየዓመቱ የግዥ ሂደቱ እንዲጓተት ማድረጉ፤

170. የመንግሥት መ/ቤቶች ከክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ና ከግዥ አፈፃፀም መመሪያ ውጭ ክፍያ ፈፅመው ዕቃ እንዲረከቡ በአገልግሎቱ በታዘዙት

መሰረት መ/ቤቶቹ ለሚገዙት ዕቃ ከመረከባቸው በፊት ቅድመ ክፍያ እንዲፈጽሙ መደረጋቸው እና የቅድመ ክፍያ እንዲፈፅሙ ሲደረግም የዕቃ አቅራቢዎች ከሚወስዱት የገንዘብ መጠን ጋር ለመንግስት መ/ቤቶቹ እኩል የሆነ ዋስትና እንዳላቀረቡ፤

171. አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ሂደት በማጠናቀቅ ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለተጠቃሚው አካላት እንዲደርሱ ሊያደርግ የሚኖርበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በአካል ከታዩ መ/ቤቶች ውስጥ 9ኙ ዕቃ ለመረከብ አቅራቢዎች ጋር ሄደው በመጋዘን የሌላቸውና ተሸጠው ያለቁ መሆናቸውን በመግለፅ ሌላ ቀጠሮ እንደተሰጣቸው፤ እንዲሁም የዋጋ ማስተካከያ እስኪሰራላቸው ድረስ መጠኑን /ብዛቱን/ ቀንሰው እንዲወስዱ የነገሯቸው መሆኑንና እስከ በጀት አመቱ ማብቂያ ድረስ ማግኘት እንዳልቻሉ፣ ለኦዲቱ በተሄደበት ወቅትም ችግሩ እንዳልተቀረፈ የገለጹ መሆኑ፤

172. በመሆኑም ሁሉም የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች በኦዲቱ የታዩትን ክፈተቶች መነሻ በማድረግና መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

የልዩ ኦዲት ስራዎች

173. በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በፍ/ቤቶች፡ በሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን እንደዚሁም በሌሎች የተለያዩ አካላት ጥያቄ 16 የልዩ ኦዲት ስራዎች ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡ በዚህም ምክንያት በመደበኛው የኦዲት ሥራ ላይ ከፍተኛ ጫና ተፈጥሮብን አልፏል፡፡.

በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ

174. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በጊዜ ገደብ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ

እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ ድንጋጌ መነሻ በማድረግ የ2005 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት እንደተጠናቀቀ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ለተገኙባቸው 87 መ/ቤቶች እና 20 የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች የማስተካከያ መርሃ-ግብር ነድፈው እንዲያሳውቁን ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም፣ እስከአሁን መርሀ-ግብሩን የላኩት 35 የፋይናንሻልና 7 የክዋኔ (ዝርዝሩን በአባሪ 2 ላይ ይመልከቱ) ኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው መ/ቤቶች ብቻ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ22 መ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ መሰረት እርምጃ ያልወሰዱ መ/ቤቶች መኖራቸው የ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ሲከናወን በተፈፀመ የክትትል ኦዲት ተረጋግጧል፡፡

175. በአንፃራዊ መልኩ በኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ የመውሰዱ ዝንባሌ ከ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በኋላ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም አሁንም ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያለመውሰድ የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑ ታውቆ እያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ም/ቤቱም በዚህ ረገድ የሚያደርገውን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር ይኖርበታል፡፡

ለኦዲተሮችና የሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ማረጋገጫ መስጠትና ማከታተልን በተመለከተ

176. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5/16 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከጥር 2005 እስከ ታህሣሥ 2006 ባለው ጊዜ ለ20 የግል ኦዲተሮችና 55 ሂሣብ አዋቂዎች አዲስ የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጥቷል፡፡

177. በሌላ በኩል ቀደም ሲል ፈቃድ በተሰጣቸው ላይም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የ528 የሂሳብ አዋቂዎችና የ72 ኦዲተሮች ዓመታዊ የሙያ የሰርትፍኬት ዕድሳት የተከናውነ ከመሆኑም በላይ የስም ዝርዝራቸውም በመ/ቤቱ ዌብ ሣይትና በጋዜጣ እንዲወጣ የተደርጎ ከዚህ ውጪ አገልግሎት

እንሰጣለን የሚሉት ሲያጋጥሙ ሕገ ወጥ በመሆናቸው ለእርምጃ አወሳሰድ እንዲያመች ኅብረተሰቡ ለመ/ቤታችን ጥቆማ የሚቀርብበትን ሥርዓት እንዲያውቀው ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም 9 የሚሆኑ የግል የኦዲት ድርጅቶችን በተመለከተ ከተገልጋዮች የቀረበውን ጥቆማ መነሻ በማድረግ ተገቢው ማጣራት ተደርጎ በ9ኙም ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ሲሆን ለወደፊቱ የሙያ ሥነ-መግባር በሚጠይቀው መሠረት አገልግሎቱን ለህብረተሰቡ እንዲሰጡ ጥብቅ ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ

178. በዚህ ረገድ ሥራዎችን ተቋሚዊ ለማድረግ ታስቦ ሥራዎቹን በቋሚነት የሚመራ ክፍል የተደራጀ ቢሆንም በውስጥ ዕድገትም ሆነ በቅጥር የሥራ መደቦቹን ማሟላት ባለመቻሉ በሥርዓታ ፆታ፣ በ HIV/AIDS እና በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከመ/ቤቱ አስፈላጊው ድጋፍ እየተሰጠ ሥራዎቹን በሚያስተባብሩ ኮሚቴዎች አማካይነት ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንና የHIV/AIDS ቀን በመ/ቤት ደረጃ ተከብሯል፡፡ በተጨማሪም የመ/ቤታችን ሴት ሰራተኞች በየሁለት ወሩ ግማሽ ቀን ቋሚ የጋራ የምክክርና የልምድ መለዋወጫ መድረክ እንዲኖራቸው ተወስኖ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ነገር ግን እንደተጠቀሰው ስራዎቹን በቋሚነት መደበኛ ሠራተኛ ተመድቦላቸው እንዲከናወኑ ለማድረግ በርካታ ጥረት ቢደረግም ባለመሳካቱ አሁንም መ/ቤቱ የተለያዩ አማራጮችን በመመልከት ላይ ይገኛል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

179. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 419 እና ለድጋፍ ሰጪ 264 በድምሩ 683 ሲሆን፣ በጥር ወር 2005 የኦዲት ሥራው ሲጀመር የነበረው የሰው ሀይል 243 ኦዲተሮችና 142 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 385 ነበር፡፡ በኦዲት ዓመቱ 85 ኦዲተሮችና 17 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 102 ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን 7 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ፣ 1 በሞት የተለየ፣ 51 ኦዲተሮችና 24 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 75 ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

180. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የኦዲት ባለሙያዎች 154 ወንዶችና 90 ሴቶች በድምሩ 244፣ የድጋፍ ሰጪ 69 ወንዶችና 91 ሴቶች በድምሩ 160 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በአጠቃላይ 404 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን፣ 281 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

የ2005 በጀት ዓመትና 2006 በጀት ዓመት

የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

181. በ2005 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ ብር 20,012,811.52 በጀት ተፈቅዶ ብር 18,096,076.69 ወይም 90.42% ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ ለ2006 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ለመ/ቤታችን ከተፈቀደው ብር 21,519,207.31 ውስጥ እስከ መጋቢት 2006 መጨረሻ የነበረው የዘጠኝ ወር ዕቅድ ብር 16,605,758.50 ሲሆን አፈፃፀሙ ደግሞ ብር 14,7277,448.87 ወይም 89%. ሆኗል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

182. መ/ቤታችን በሕገ-መንግሥትና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም፣ በተለይ ከሰው ሀይል ፍሰት ጋር በተያያዙ ተግዳሮቶች ምክንያት ያሰበውን ያህል ውጤት ማስገኘት አልቻለም፡፡ በሥራ ላይ እየተፈታተኑን ከሚገኙ ተግዳሮቶች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

183. ባለፉት ዓመታት በተደረገው ከፍተኛ ጥረት የኦዲት ሽፋን ያደገ ቢሆንም ኦዲቱን በሚፈለገው ጥልቀትና ጥራት ለማከናወን የሚያስችል በቂ ክህሎትና ልምድ ያለው ባለሙያ ከደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ማነስ ጋር በተያያዘ ለማቆየትም ሆና ለመቅጠር ባለመቻሉ እስከ አሁን በተገኙ ውጤቶች ቀጣይነትና ሊሠሩ በታቀዱት ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ሥጋት ፈጥሯል፡፡ በተለይ የቁልፍ የሰው ሀይል ፍሰቱ ችግር ከወትሮ በተለየ ሁኔታ በመባባሱ ለም/ቤቱ ጭምር አሳሳቢነቱን በማሳየትና በማስረዳት ችግሩ መፍትሄ እንዲያገኝ ጥረት የተደረገ ቢሆንም እስከ አሁን ሊፈታና መፍትሄ ሊያገኝ አልቻለም፡፡

184. ይህ ችግር በበርካታ የመንግስት መ/ቤቶች የሚታይና አጠቃለይ መፍትሄ የሚሻ ቢሆንም ከመ/ቤታችን ተልዕከና ተልዕኮውንም ለማስፈፀም ከሚያሰፈልገው የሰው ሀይል አንፃር አንድ ዓይነት የሙያ ስብጥር የሚጠይቅና ሙያው ደግሞ በገበያ ላይ ከፍተኛ ተፈለጊነት ያለው በመሆኑና እነኚህን ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎችን በቀላሉና በአጭር ጊዜ ማፍራት ስለማይቻል ችግሩን ልዩ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ ከወዲሁ ልዩ ትኩረት አግኝቶ መፍትሄ ካልተሰጠው በአፈፃፀማችን ላይ የሚያስከትለው ችግር የከፋ ይሆናል፡፡

185. ለኦዲቱ ሥራ የሚደረገው ትብብር በአብዛኛው መሻሻል ያሳየ ቢሆንም ቁጥሩ በማይናቅ ደረጃ አሁንም በአንዳንደ መ/ቤቶች ያለመተባበር (በወቅቱ የሥራ ቦታ ያለማመቻቸትና መረጃ ያለመስጠት) ችግሮች የሚታይ በመሆኑ መ/ቤቶቹ በፍጥነት እነኚህን ችግሮች በማስወገድ ሕጋዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

186. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ እስከ መስከረም 30 ሂሳባቸውን በመዝጋት ለኦዲት ማቅረብ ቢኖርባቸውም 92 መ/ቤቶች ወይም 69% (ዝርዝሩን በአባሪ 1 ይመልከቱ) የሚሆኑት ሂሳባችውን ከመስከረም 30/2006 በኃላ የዘጉ በመሆኑ የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በታሰበው ጊዜ ማጠናቀቅ ካለመቻሉም በላይ የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በመርሀ-ግብራችን መሠረት እንዳንጀምርና ዓመታዊ ሪፖርታችንንም በወቅቱ እንዳናዘጋጅ ከፍተኛ እንቅፋት ሆኖብን አልፏል፡፡

187. ይህ ሁኔታ በማጋጠሙ ኦዲቱን አቋርጦ መውጣት የሚቻል ቢሆንም ከማቋረጥ ይልቅ የየመ/ቤቶቹን የበላይ ኋላፊዎች በተደጋጋሚ በማነጋገር የዘመኑን ኦዲት የማጠናቀቅ ኃላፊነታችንን ተወጥተናል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ የሕግ ጥሰት በመሆኑ ለወደፊቱ እንዳይደገም መ/ቤቶች ከወዲሁ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ሂሳባቸውን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ ባስቀመጠው የሕግ የጊዜ ገደብ ውስጥ ዘግተው ለኦዲት ማቅረብ እንደሚኖባቸው በጥብቅ አሳስበናል፡፡ ይህን ባያደርጉ ግን ለወደፊቱ የኦዲት ጥያቄውን ተቀብለን እንደማናስተናግድ ሁሉም መ/ቤቶች ከወዲሁ እንዲያውቁ ሠርኩላር ተላልፎላቸዋል፡፡

188. በአብዛኛው መ/ቤቶች የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍሎች አሁንም በማዋቅር፤ በክህሎትና በዕውቀት በሚገባ ባለመደረጀታቸውና አንፃራዊ ነፃነታቸው ተጠብቆ እንዲሠሩ ባለመደረጉ ወይም ባለመፈቀዱ የውጪ ኦዲቱ ከውስጥ ኦዲት ሥራ

ማግኘት የሚገባውን ፋይዳ ሊያገኝ አልቻለም፡፡ በሌላ በኩል ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ጥረቶች በመደረጋቸው የተወሰነ ለውጥ ቢኖርም አሁንም የታሰበውን ወጤት ባለማስገኘቱ ጥረቱ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

189. መሻሻሎች ያሉ ቢሆንም አሁንም በርካታ ኦዲት ተደራጊዎች ከመ/ቤታችን በሚላኩ የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠትና በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረትም በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ የማስተካከያ እርምጃ ያለመውሰድ ችግር ቀጥሏል፡፡ ይህ ሁኔታ በዚህ መልኩ ሊቀጥል ስለማይገባና ከፍተኛ ተጠያቂነትን ጭምር የሚያስከትል በመሆኑ የሚመለከታቸው አስቀድው ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንድወስዱ ይመከራል፡፡ በም/ቤቱም በኩል የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ የማስተካከያ እርምጃ በማይወስዱ ኦዲት ተደራጊዎች ላይ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ

190. የሰው ሀይል ፍሰቱ ፈተኝ ቢሆንም ችግሩ በሚመለከተው አካል ተገቢውን መፈትሄ እንደሚያገኝ ታሳቢ በማድረግ በ2006 በጀት ዓመትም የሂሳብ ኦዲቱ ሽፋን 100% ሆኖ እንዲቀጥል ታቅዷል፡፡ ነገር ግን ካለፉት ዓመታት በተለየ ሁኔታ የኦዲት ጥራት የሁሉም ኦዲት ፈፃሚ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጎ የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ ተነድፏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከጥር 2006 እስከ ታህሣሥ 2007 ድረስ 28 የክዋኔ ኦዲቶችን በማከናወን 22 ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል፡፡ በሌላ በኩል ከጥር 2006 እስከ ታህሣሥ 2007 ድረስ በ300 የመሠረታዊ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረደዎችና የሴክተር ቢሮዎች የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡

191. በዚሁ መሠረት ከየካቲት እስከ መጋቢት 30/2005 ባሉት ሁለት ወራት ጊዜ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በ49 መ/ቤቶች እና 5 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደግሞ ካለፈው ዓመት የዞሩ 6ቱን ጨምሮ 20 የክዋኔ ኦዲቶች እና 61 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲቶች

ተጀምረው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በላይ በአጠቃላይ የኦዲቱ ሥራ እስከ አሁን በታቀደው መሠረት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

192. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽኑ እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት አስደርጎ በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊው የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

193. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2005 በተከናወኑ ኦዲቶች የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረበ ስለሆኔ ዝርዝሩን ከዚያው መመልከት ይቻላል፡፡

ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶች የሂሣብ መግለጫ ሁኔታ

194. በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 69 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በውጭ መንግሥታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሣብ ደግሞ 145 በድምሩ 214 ኦዲቶች ተከናውኗል፡፡

195. በእነዚህ ሪፖርቶች ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፣ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Unqualified opinion) 105፣ ነቀፌታ ያለበት

አስተያየት (Qualified opinion) 99፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት (Disclaimer opinion) 9 እና አስተያየት ያልተሰጠበት 1 በድምሩ 214 ናቸው፡፡

196. በሌላም በኩል መ/ቤታችን ባለው መረጃ መሠረት ከሁለት ዓመታት በላይ ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት ያላስደረጉ 40 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይገኛሉ፡፡

የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን
የሥራ እንቅስቃሴና ያጋጠሙ ችግሮች

197. የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 126/1969 የተቋቋመ ሲሆን፣ ዓላማው፤ የመንግስት ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዙ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት ማበርከት ነው፡፡

የኮርፖሬሽኑ የዕቅድ ክንውን

198. በ2005 በጀት ዓመት መጀመሪያ በነበረው 112 የሰው ኃይል 235 ኦዲቶችን ለማድረግ አቅዶ 229 ኦዲቶችን ወይም የዕቅዱ 97.44% ለመፈጸም ችሏል፡፡

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

199. ኮርፖሬሽኑ በ2005 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 14.78 ሚሊዮን ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 15.51 ሚሊዮን ገቢ አግኝቷል፡፡ በሌላም በኩል ብር 8.39 ሚሊዮን ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 8.22 ሚሊዮን ወጪ ያደረገ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ የብር 5.10 ሚሊዮን የተጣራ ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ማጠቃለያ

200. በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2005 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው ኦዲት በሂሳብ ምርመራ ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የተያዙትን ጨምሮ የኦዲት ሽፋኑን

98.57% ደርሷል፡፡ የኦዲት ዕቅድ ክንውናችንም የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት 98.57% እና የክዋኔ ኦዲቱም 20 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት በታቀደው መሰረት 20 ቹም (100%) ሲጠናቀቁ ሌሎች በዳሰሳና ቅኝት ደረጃ የሚገኙ 6 ክዋኔ ኦዲቶች በዕቅዱ መሠረት ወደ ቀጣዩ ዓመት የተላለፉ ሲሆን፤ የመሠረታዊ አገልግሎት ክለላ ኦዲት 298 ታቅዶ 281 ወይም 94.29% ተከናውኗል፡፡ በአጠቃላይ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን ሽፋን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ማድረስ በመቻሉና ውዝፍ የኦዲት ሥራ ባለመኖሩ ወቅታዊ የኦዲት መረጃን ማመንጨት ተችሏል፡፡ ይህ ውጤት አሁንም ከፍተኛ የባለሙያ ፍሰት ባለበት ሁኔታና በርካታ የልዩ ኦዲት ስራዎች ጫና ውስጥ በመሆን የተገኘ ውጤት መሆኑ ግን በትኩረት ሊታይ ይገባል፡፡

201. ውዝፍ የኦዲት ሥራ አለመኖሩና ሁሉንም የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶችን በየዓመቱ ኦዲት በምናደርግበት ደረጃ ላይ መገኘታችን የአሠራር ክፍተቶችን በፍጥነት በመለየት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ዕድል የሚሰጠን ቢሆንም፤ በተደጋጋሚ የሚታዩ ተመሳሳይ ነገር ግን ትኩረት ቢሰጣቸው ኖሮ ሊወገዱ የሚችሉ ግድፈቶች በዚህም ዓመት ማስቀረት አለመቻላችን አሁንም የቱን ያህል ትኩረት ለዚህ ጉዳይ ልንሰጥ እንደሚገባ አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የሚመለከታቸው ሁሉ የተጠናከረ ክትትል ሊያደርጉና እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ ዝርዝር የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱ በሁለት ጥራዝ እንደዚሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ደግሞ በ20 ጥራዝ ተዘጋጅቶ፤ ለአፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት የተላከ በመሆኑ፤ በም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚዎች በኩል በጥልቀት ተመርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

202. እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ እየተንከባለሉ የመጡት ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተደጋጋሚ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች፤ እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች በሁሉም ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ልዩ ትኩረት አግኝተው ሊታረሙና ሊስተካከሉ ይገባል፡፡

203. በሌላ በኩል ከመንግሥት ግንባታዎች ጋር በተያያዘ በወቅቱና በተያዘላቸው በጀት ያለመጠናቀቅ፤ መፍትሔ ሣያገኙ ለረጅም ወራትና ዓመታት ጭምር የግንባታ ሂደታቸው የቆሙ ፕሮጀክቶች አፋጣኝ እርምጃ የሚያሻው በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፤፤

204. በተጨማሪም በሚቀርቡት የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በሚሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶች መሠረት እርምጃ የማይወስዱ አካላትን በተመለከተ ም/ቤቱ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ከ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ጀምሮ ተገቢ ነው የሚለውን እርምጃ በመውሰድ ችግሩን ለማቃለል ጥረቱን ይበልጥ ሊያጠናክር ይገባል፡፡

205. መሻሻል ሲገባው እየባሰበት የመጠው የባለበጀት መ/ቤቶች ሂሳብን በወቅቱ ዘግቶ ለኦዲት ያለማቅረብ ጉዳይ በአንክሮ ሊታይና ተገቢው ህጋዊ እርምጃ የሚያሻው ነው፡፡ ይህን በተመለከተ በእኛ በኩል ተገቢው እርምጃ የተወሰደ ቢሆንም በም/ቤቱም ሆነ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ጉዳዩ በአንክሮ ሊታይ አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

206. በመጨረሻም እስከ አሁን የተገኘውን ውጤት ጭምር ወደ ኋላ ለመመለስና የወደፊቱን አፈፃፀም ሊጎዳ በሚችል መጠን በሁሉም ደረጃ መ/ቤቱን እየተፈታተና የሚገኘውን የሠራተኛ ፍሰት ችግር ለማቃለል ም/ቤቱ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ በአክብሮት እየጠየቅሁ በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉና ዘግይተው ለኦዲት ያቀረቡ መ/ቤቶች

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	
1	1	ግብርና ሚኒስቴር	24/04/06
2	2	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	**ህዳር 2006**
3	3	የውሃ፣ የመስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	1/4/2006
4	4	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	ህዳር/2006
5	5	የብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	24/4/2006
6	6	የህብረት ስራ ኤጀንሲ	11/4/2006
7	7	የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትአስተዳደር	7/2/2006
8	8	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	27/2/2006
9	9	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	29/2/2006
10	10	የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት	4/42006
11	11	የኢትዮጵያሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዮት	14/4/2006
12	12	የብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ አስተዳደር	15/02/2006
13	13	የአማኑኤል የአዕምሮ ሰፔሻላይዝድ ሆሰፒታል	28/02/2006
14	14	የኢ.ት.የምግብ፤የመድሀኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	10/4/2006
15	15	የኢ.ት.የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	2/3/2006
16	16	የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን	16/03/2006
17	17	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	7/5/2006
18	18	የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን	28/02/2006
19	19	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ	22/02/2006
20	20	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን	**ህዳር/2006**

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
		ሚኒስቴር	
21	21	የኢትዮጵያ ጤናና ሥነ ምግብ ኢኒስቲትዩት	1/4/2006
22	22	የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ	4/3/2006
23	23	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን	27/03/2006
24	24	አለርት ሆስፒታል	2/2/2006
25	25	ማዕድን ሚኒስቴር	ኅዳር 2006
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	
26	1	የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	4/3/2006
27	2	የንግድ ሚኒስቴር	21/04/06
28	3	የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት	20/02/06
29	4	የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ	26/02/06
30	5	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	2/5/2006
31	6	የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	14/02/06
32	7	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ	14/02/06
33	8	የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል	26/02/06
34	9	የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	23/03/06
35	10	የፍትህና የሕግ ሥርአት ኢንስቲትዩት	20/2/06
36	11	ብሔራዊ መረጃ ደህንነት	4/2/2006
37	12	የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ	14/4/06
38	13	የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማስልጠኛ ማዕከል	5/3/2006
39	14	የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን	11/2/2006
40	15	የፌደራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	17/03/06
41	16	ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	26/3/2006
42	17	ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር	3/4/2006
43	18	የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት	25/3/06
44	19	ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት	15/05/06
45	20	የውጭ ጉዳይ ሚ/ር	5/2/2006
46	21	ብሔራዊ አክርዲቴሽን ጽ/ቤት	5/3/2006
47	22	የሀገር መከላከያ ሚ/ር	26/02/2006
48	23	የታለቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ምክር ቤት ጽ/ቤት	19/02/2006

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	
49	1	አምቦ ዩኒቨርስቲ	18/02/06
50	2	አዳማ ሳ/ቴ ዩኒቨ.	28/02/06
51	3	ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ	9/3/2006
52	4	አሶሳ ዩኒቨርስቲ	30/03/06
53	5	ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ	10/2/2006
54	6	ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ	4/2/2006
55	7	ጎንደር ዩኒቨርስቲ	4/2/2006
56	8	ሐዋሳ ዩኒቨርስቲ	13/02/06
57	9	ወሎ ዩኒቨርስቲ	13/03/06
58	10	ወልድያ ዩኒቨርስቲ	15/02/2006
59	11	ቡሌ-ሆራ ዩኒቨርስቲ	21/03/06
60	12	ዲላ ዩኒቨርስቲ	14/4/06
61	13	ሠመራ ዩኒቨርስቲ	11/4/2006
62	14	ትምህርት ሚኒስቴር	21/04/06
63	15	ወላይታ-ሶዶ ዩኒቨ.	6/2/2006
64	16	አርባ ምንጭ ዩኒቨ.	13/03/06
65	17	አክሱም ዩኒቨርስቲ	18/02/06
66	18	ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨ.	4/3/2006
67	19	አ.አ.ሳይንስና ቴ. ዩ.	17/04/06
68	20	ሳይንስና ቴክ. ሚ/ር	18/04/06
69	21	ከፍ. ትም.ጥና አ. ኤጀንሲ	12/4/2006
70	22	የኢ. ልማት ምርምር ኢኒስቲትዩት	19/03/06
71	23	ጅማ ዩኒቨርስቲ	8/5/2006
72	24	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ	15/02/06
		የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	
73	1	የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት	01/04/2006
74	2	ወለጋ ዩኒቨርስቲ	21/02/2006
75	3	የሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር	11/03/2006
76	4	የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት	11/03/2006
77	5	የቤተ መንግስት አስተዳደር	19/02/2006
78	6	የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን	8/02/2006
79	7	የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት	24/02/2006

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
80	8	የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	22/02/2006
81	9	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	26/03/2006
82	10	የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በጀት	3/3/2006
83	11	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ	18/03/06
84	12	የኢ.ት/ ፕሬስ ድርጅት	4/2/2006
85	13	የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት	28/02/06
86	14	የኢ.ት/ ካርታ ስራባለስልጣን	11/2/2006
87	15	የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	20/02/06
88	16	የብሄራዊ የስነ ልክ ኢንስቲትዩት	4/2/2006
89	17	ደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ	6/2/2006
90	18	የመንግስት የፋይናንስ ድርጅት ኤጀንሲ	21/02/06
91	19	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ጥር/2006
92	20	የመንግሥት አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ/2005 በጀት/	

የ2005/2006 ፋይናንሻልና ህጋዊነት ኦዲት የድርጊት መርሃ ግብር የላኩ መ/ቤቶች ዝርዝር

ተራ ቁ.	የመ/ቤቱ ስም
1.	አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ
2.	በፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ
3.	ብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት
4.	የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ
5.	ውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴ
6.	ኤች. አይ.ቪ. ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት
7.	የእንስሳት መድኃኒት መኖ አስተዳዳርና ቁጥጥር
8.	ህብረት ሥራ ኤጀንሲ
9.	የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ
10.	ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት
11.	መከላከያ ሚኒስቴር
12.	የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት
13.	ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር
14.	ንግድ ሚኒስቴር
15.	ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

ተራ ቁ.	የመ/ቤቱ ስም
16.	ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት
17.	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ
18.	የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ
19.	በህር ዳር ዩ ኒቨርሲቱ
20.	አክሱም ዩኒቨርሲቲ
21.	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
22.	የመንግሥት ግዥ ንብረት ማስወገድ
23.	ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች
24.	ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
25.	ገቢዎችና ጉምሩክ ቀረጥ ነፃ
26.	ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
27.	ኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን
28.	ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ
29.	ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ
30.	ጂማ ዩኒቨርሲቲ
31.	ብሔራዊ የሜቲናዋሮሎጂ ኤጀንሲ
32.	ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ
33.	ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
34.	ትምህርት ሚኒስቴር
35.	መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ

የ2006 የክዋኔ ኦዲት የድርጊት መርሃ ግብር
የላኩ መ/ቤቶች ዝርዝር

ተራ ቁ.	የመ/ቤቱ ስም
1.	ትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት
2.	ኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት
3.	ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር
4.	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
5.	በፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ
6.	ገቢዎችና ጉምሩክ ታክስ መረጃ
7.	ገቢዎችና ጉምሩክ ታክስ ኦዲት